# ኃይላችን
# የእግዚአብሔር መንፈስ

**ክፍል 2**

በ ጃኪይ ኦስክ

## ከሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የተወሰደ ታሪክ

ትምህርት 1: *ዝምታው — ያለልዩነት*
ትምህርት 2: *በመንፈስ ቅዱስ መላክ —የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ*
ትምህርት 3: *እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? —ሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ*
ትምህርት 4: *ወደ አህዛብ ሂዱ — መከራ*
ትምህርት 5: *ሰሙ - ሮም*

"…ቃልህን በልቤ ሰወርኩ…"
*መዝሙር* 119:11

በቴንዝፓዎር ፐብሊሽንግ የተዘጋጀ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው ©2015 በክሮስኮኔክት ሚኒስትሪ

ይህንን ጥናት ያለ አዘጋጁ የፅሁፍ ፈቃድ ማንኛውንም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማባዛት ሆነ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1962 ዓ፡፡ ም፡፡  እትም የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡፡

# መቅድም

ቀሪውን የህይወታችሁን ዘመን መልክ የሚያስይዘውን የጥናት ጉዞ ቀጥላችኋል፡፡ ከዚህ ጥናት ለህይወታችሁ የምታረፉት ነገር ለጥናቱ ካላችሁ መሰጠትና ትኩረት ጋር የሚያያዝ ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥናት የምታሳዩት መሰጠት እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ በተናገራቸው ተስፋዎች ህይወታችሁ የተሞላ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ስለዚህ ይህንን ጥናት ስታጠኑ በጥናታችሁ ሊያግዟችሁ የሚችሉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ሊኖሯችሁ ይገባል እነርሱም፡

1. *"ኃይላችን የእግዚአብሔር መንፈስ"- ክፍል 2* የሚለው የጥናት ክፍል ጥራዝ
2. አዲሱ የአማርኛ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ፡፡ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ የምትገዙ ከሆነ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ የሚከተሉት ነገሮች ያካተተ ቢሆን መልካም ነው፡፡
   ሀ፡፡ በእያንዳንዱ ገጽ ማጣቀሻ ጥቅሶችን የያዘ
   ለ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማውጫ በጀርባው በኩል የያዘ እና
   ሐ፡፡ ጥቂት መሰረታዊ ካርታዎችንም በጀርባ በኩል ባሉት ገጾች ላይ የያዘ ቢሆን ይመረጣል፡፡
3. እስኪርብቶ ወይንም እርሳስ
4. ማስታወሻ መፃፊያ ካርድ

መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተጠቀሱት ሶስት ነገሮች ቢኖሯችሁ ጥናታችሁን በአግባቡና በተሳካ ሁኔታ ማከናወን ትችላላችሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ ይህ የጥናት ክፍል የመጀመሪያችሁ ከሆነ በቅድሚያ *"የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኝት"* የሚለውን የጥናት ክፍል ብታጠኑ መልካም ነው፡፡ ይህ የጥናት ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁን በተሳካ መልኩ እንድታከናውኑና ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ መሆን የምትችሉበትን መንገድ የሚጠቁም የጥናት ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የጥናት ክፍል *"ኃይላችን የእግዚአብሔር መንፈስ ክፍል 2"* የሚለውን የጥናት ክፍል ለማጥናት የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳችሁ የራሳችሁ ንብረት በመሆኑ ውስጣችሁን የነካውን ክፍል በማስታወሻችሁ ያዙ፣ በማርከራችሁ ምልክት አድርጉበት፣ አስምሩበት፣ አክብቡበት፣የቀስት

ምልክት አድርጉበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሞባይል ስልኮችን፣ታብሌቶችን እንደዚሁም ኮምፒውተሮችን በመጠቀም የተለያዩ አዳዲስ ሃሳቦችን፣ ጥያቄዎችን፣ መያዝ ትችላላችሁ፡፡

ይህ የጥናት ክፍል በጽሑፍ መልክ የተዘጋጀ በመሆኑ ብቻችሁን ሆናችሁም ማጥናት ትችላላችሁ፡፡ ለጥናታችሁ አስፈላጊውን ትኩረትና ጊዜ መስጠት እራሳችሁን ካስለመዳችሁ ጥናታችሁን ያለምንም ችግር መጨረስ ትችላላችሁ፡፡ ይህ ጥናት በጽሑፍ ተጠርዞ የተዘጋጀ በመሆኑ ብቻችሁን እያነበባችሁ ማጥናት ትችላላችሁ፡፡ የሚጠበቅባችሁ ይህንን ጥናት ስታጠኑ ለጥናቱ በቂ ጊዜ መስጠት ነው፤ ይህንን ካደረጋችሁ ጥናቱን ያለምንም ችግር መጨረስ ትችላላችሁ፡፡ ጥናታችሁን ስትቀጥሉም አዳዲስ ሃሳቦችን ልታገኙ ትችላላችሁ፣ አዳዲስ መረዳቶችን ልታገኙ ትችላላችሁ፣ አንዳንድ አስቸጋሪና መልስ የሚሹ ጥያቄዎች ሊገጥሟችሁ ይችላል፡፡ የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ወደ ጥናት ክፍላችሁ ስትመጡ ሌሎችን ጓደኞቻችሁን ጋብዙ፡፡

ጥናታችሁ አስደሳች እንዲሆንና እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ሲናገራችሁ መስማት ይሆንላችሁ ዘንድ እንመኛለን፡፡ ይህ ጥናት መድኃኒታችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠውን እውነት የምትረዱበት ይሁንላችሁ፡፡

# ትምህርት አንድ

# ዝም አሉ

## የሐዋሪያት ሥራ 10-12 — ያለልዩነት

---

**የትምህርት አንድ ቅኝት**


ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1:  የሐዋሪያት ሥራ 10-12

- የቆርኔሎዎስ ራዕይ
- የጴጥሮስ ራዕይ
- አድልዎ የለም
- በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምላሽ
- ስደት
- የጴጥሮስ እስራት እና ከእርስ ማምለጥ

## መግቢያ

የኢየሩሳሌም መሪዎች ኢየሱስ ባስተማረው አዲስ የህይወት ስርአት ግራ ተጋብተው እና ተናውጠው አልፈዋል፡፡ አሁን ደግሞ በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውሳኔ በጣም ታውከዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባሳለፈችው አዲስ ውሳኔ በጣም ተረብሸዋል፡፡ እግዚአብሔር በጴጥሮስ ህይወት ከሰራው ስራ የተነሳ እግዚአብሔር ሳያዳላ የንሰሃን እድል ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ እንደሰጠ አረጋግጧል (የሐዋሪያት ሥራ 11:18)፡፡

በዚህ የጥናት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱን ውሳኔ ውጤት በሰፊው ትመለከታላችሁ፡፡ ይህንን ትምህርት ስትከታተሉ የአይሁዶችን ያለፈ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ አስገቡ ፡፡ በምድረ በዳው ውስጥ በነበሩበት ወቅት ምን ነበር የተማሩት? እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገባው ምን አይነት ቃል ኪዳን ነበር? ህጉ ምን ነበር የሚገልጠው? ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ራዕይ የተቀበሉበት መቼት እንደዚህ ቀርቧል፡፡

“ወደ ዓለም ሂዱ…” ከሚለው የኢየሱስ ቃል አላማና ፣ዋጋ አንጻር እንደገና መታየትና መመርመር ያለባቸውን በህይወታችሁ ውስጥ ያሉ ሁኔታዎችን አጢኗቸው፡፡

“…ዝም አሉና…እግዚአብሔርን አከበሩ!”

## ትምህርት 1

### ክፍል 1

### ትምህርት

በሐዋሪያት ሥራ 9:31 ውስጥ ገሊላን ይዞ በደቡብ ይሁዳ ላሉት ክርስቲያኖች የሰላም ጊዜ እንደሆላቸው እንመለከታለን። በዚህ የሰላም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ________________________ሆና ነበር። አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ____________________________ ነበር።

ምዕራፉ የሚጠናቀቀው ስለ ጴጥሮስ ሁለት ታሪኮችን በመተረክ ነው። የመጀመሪያው ታሪክ (ከቁጥር 32-35) ባለው ክፍል ውስጥ የሚገኘው ኤንያ ስለሚባለው ከሽባነት ስለተፈወሰው ሰው የሚናገረው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ (ከቁጥር 36-42) ባለው ክፍል ውስጥ ስለምትገኘው ዶርቃ የሚል የስም ትርጓሜ ያላት ከሞት ስለተነሳችው ጣቢታ የሚናገረው ክፍል ነው። እርሷ በምትኖርበት አካባቢ የሚኖሩ አማኞች መሞቷን ሲሰሙ ወደ ጴጥሮስ መልእክት ላኩበት። ጴጥሮስም ህይወቷን  እንደገና ወደ መለሰላት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

በዚህ ስፍራ ጴጥሮስ ኢየሱስ ሲያገለግል የነበረውን አይነት አገለግሎት ነበር ያገለገለው። በሉቃስ 8:51-56 ኢየሱስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት ሊያስነሳት በሄደ ጊዜ አስከትሎ የሄደው ጴጥሮስን፣ያዕቆብንና ዮሐንስን ነበር ። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ አብረውት መኖራቸውን ታሳቢ በማድረግ ማርቆስ ጓደኞቹ ወደ እርሱ ይዘውት የመጡትን ሽባ ሰው ኢየሱስ እንደ ፈወሰው ይነግረናል (ማርቆስ 2:1-12)። (ቁጥር 11) ኢየሱስ ሽባውን ሰው የፈወሰበትን መንገድና ጴጥሮስ ኤንያን ሲፈውስ ባደረገው ነገር መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ልብ በሉ። ጴጥሮስ ኢየሱስ ሲያደርግ የተመለከተውን አይነት አገልግሎት ነበር ተግባራዊ ያደረገው።

### መግቢያ

የሐዋሪያት ሥራ 10 ስለ ጴጥሮስ ሌላ አስደሳች ነገር ይነግረናል። ይህ ታሪክ የተከናወነው ጴጥሮስ ከሚኖርባት ኢዮጴ በስተ ደቡብ 48 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘውና ቆርኔሌዎስ

በሚኖርባት የቂሳርያ ከተማ ነው፡፡ ቂሳርያ በታላቁ አውግስጦስ ቄሳር ስም የተሰየመች የሮማውያን ወታደራዊ ማእከል የሆነች ከተማ ስትሆን ቆርኔሌዎስ ደግሞ ከአህዛብ ወገን ነበር፡፡

**የቤት ስራ**: የሐዋሪያት ሥራ 10:1-7 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ከቁጥር 1-2 ባለው ክፍል ውስጥ ስለ ቆርኔሌዎስ ምን እንማራለን?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ቆርኔሌዎስ ከእለታት አንድ ቀን ምን ገጠመው (ቁጥር 3)?

_______________________________________________

_______________________________________________

3. መልአክ ተገለጠ አናገረው፡፡ ለመሆኑ መልአኩ የነገረው ሁለት ነገሮች ምን እና ምን ነበሩ (ቁጥር 4-5)?

   ሀ.____________________________________________

   ለ.____________________________________________

   (በቁጥር 7 እና 8) ውስጥ ቆርኔሌዎስ ምን ያደርግ እንደ ነበረ ነው የተነገረን?

_______________________________________________

_______________________________________________

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 10:9-23 አንብቡ፡፡

**መልመጃ** : ራዕይ ቁጥር ቁጥር 2

1. በቀጣዩ ቀን ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ወደ ከተማይቱ ሲቀርቡ ምን ነበር የተከናወነው (ቁጥር 9-10)?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. እስቲ የጴጥሮስን ራዕይ በራሳችሁ አባባል በአጭሩ ግለፁ (ቁጥር 11-15):

______________________________________________

______________________________________________

2. ጴጥሮስ በተመለከተው ራዕይ አርዶ እንዲበላቸው የታዘዘው ንጹህ ያልሆኑ እንሰሳትን ነበር። እነዚህን እንሰሳት የሌዋውያን መጽሐፍ የማይበሉ እና ንጹህ ያልሆኑ እንሰሳት እንደሆኑ ይናገራል። ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 ተመልከቱ። ለጴጥሮስ እነዚህን እንስሳት አርዶ እንዲበላ በራዕይ የተላለፈለት ትእዛዝ ከዚህ ህግ ጋር የሚጋጭ ነበር። በቁጥር 15 በራዕይ የተገለጠለት ድምጽ ምን እንዲያደርግ ተናገረው?

______________________________________________

______________________________________________

ቀጥሎ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በቁጥር አስራ አምስት ላይ ለተገለጸው ነገር ምን አይነት መረዳት እንዲኖራችሁ ያደርጋሉ?

ሀ. ማቴዎስ 15:11፤ 18-20

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ለ. ዮሐንስ 15:3

______________________________________________

ሐ. ሮሜ 14:17

______________________________________________

3. ጴጥሮስ ስላየው ራዕይ እያሰላሰለ ሳለ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ወደ ደጅ ቀረቡ (ቁጥር 17):

______________________________________________

4. እነ ማን ነበሩ ወደ ደጁ የቀረቡት (ቁጥር 18)?

______________________________________________

5. የራዕዩ ድምጽ ተገለጠ። ____________________ነበር (ቁጥር 19)። መንፈስ ለጴጥሮስ ምን ነገረው (ቁጥር 19-20)?

ሀ.________________________________________________________

ለ.________________________________________________________

ሐ._______________________________________________ልኬያቸዋለሁ፡፡

6. ጴጥሮስ ከሰገነቱ ላይ ወርዶ ሰዎቹ የመጡበትን ምክንያት ጠየቃቸው፡፡ ሰዎቹ ለጴጥሮስ የሰጡት ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 22)?

   ሀ. ማንን ወክለው ነበር የመጡት?

   ______________________________________________________

   ለ. በምን መልኩ ነበር ሁኔታውን የገለጹለት?

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ሐ. ወደ ጴጥሮስ ምን አይነት መልእክት ነበር ይዘው የመጡት?

   ______________________________________________________

7. የጴጥሮስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 23)?

   ______________________________________________________

**በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁ የግል አስተያየት፤** ይህንን ታሪክ ስትመለከቱ ምን አይነት ሃሳብ ወይንም መረዳት ወደ ውስጣችሁ ይመጣል?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

## ክፍል 2

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 10:23-48 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**:

1. ቆርኔሌዎስ በቤቱ ከማን ጋር ሆኖ ነበር የጴጥሮስን መምጣት ይጠባበቅ የነበረው (ቁጥር 24)?________________________________________________

   ______________________________________________________

2. እስቲ የነበረውን ሁኔታ ግለጹ

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

3. ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲገባ በጣም ብዙ ህዝብ ነበር ተሰብስቦ የጠበቀው (ቁጥር 27)። በአይሁድ ሕግ ክልክል የነበረው ምን ነበር (ቁጥር 28)?

___________________________________________________________

ጴጥሮስ ራዕዩን እንዳይታዘዝ ያደረገው ከህጉ ተቃራኒ የሆነበት ነገር ምን ነበር (ቁጥር 28)?

___________________________________________________________

___________________________________________________________

4. እግዚአብሔር ያስተማረው ነገር ምንድነው?

___________________________________________________________

5. ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስን ምን ጠየቀው (ቁጥር 29)?

___________________________________________________________

ቆርኔሌዎስ መልእክተኞችን ወደ ጴጥሮስ የላከበትን ምክንያት ነገረው። በመጀመሪያ ስለተመለከተው ራዕይ ተረከለት። በቁጥር 33 ላይ እንደዚህ አለው "ስለዚህ ያን ጊዜ ወደ ___________________ ላክሁ፥ አንተም በመምጣትህ ___________________ አድርገሃል። እንግዲህ አንተ ___________________ ዘንድ የታዘዝኸውን ሁሉ ___________________ እኛ ሁላችን አሁን ___________________ ፊት በዚህ አለን።"

6. ጴጥሮስ መናገር ሲጀምር ምን በማለት ነበር የጀመረው (ቁጥር 34-35)?

___________________________________________________________

___________________________________________________________

7. ጴጥሮስ "ታውቃላችሁ" በሚል ቃል ነበር ንግግሩን የጀመረው። ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ምን ነበር የሚያውቁት (ቁጥር 36)?

___________________________________________________________

___________________________________________________________

8. ሌላስ የሚያውቁት ምን ነበር (ቁጥር 37-38)?

___________________________________________________________

___________________________________________________________

___________________________________________________________

9. እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያሉ ሰዎች ስለሚያውቁት ነገር ጴጥሮስ ምን ነበር ያለው (ቁጥር 39-41)?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

_________________________________________________________

10. የአይን ምስክር የሆኑት ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነበር ትእዛዝ የተሰጣቸው (ቁጥር 42)?

    ሀ.___________________________________________________

    ለ.___________________________________________________

11. መልእክታቸው ምን መሆን ነው ያለበት (ቁጥር 43)?

    __________________________________________________________

12. ጴጥሮስ ሲናገር ሳለ ምን ሆነ ?

    ሀ. ቁጥር 44:

    ___________________________________________________

    ለ. ቁጥር 45:

    __________________________________________________

    ሐ. ቁጥር 46:

    __________________________________________________

13. ከቁጥር 47-48 ባለው ክፍል ውስጥ ጴጥሮስ ምን ነበር ያዘዘው?

    __________________________________________________________

    __________________________________________________________

**ትምህርት**

የጴጥሮስ ራዕይና ጉብኝት ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነበር፤ ምክንያቱም በቁጥር 34 እና 35 ላይ እንደዚህ በማለት ተናግሯል፡ "________________________ አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ፦ _______________________ ለሰው ፊት __________________ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ___________________የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት ____________________________::"

ይህንን ቃል የሚያነቡ አንዳንድ ሰዎች እንደዚህ በማለት ሊናገሩ ይችላሉ፡ "መልካም! እንግዳው እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ይቀበላል ማለት ነው።" ይህንን ንግግር ለመናገር ግን እንደ ጴጥሮስ ሳለ በአይሁድ ስርአት ውስጥ ሳደገ ሰው ቀላል አይደለም። ምክንያቱም የህጉ ተቃራኒ ሃሳብ በመሆኑ ነው። እየሆነ ያለው ነገር በሙሉ ከህጉ ተቃራኒ ነበረ። ጴጥሮስ

ከአህዛብ ጋር ህብረት እያደረገ ነው። አህዛብ የሆኑ እንግዶችን ተቀብሎ አስተናግዷል፤ እንዲሁም አህዛብ በሆኑ ሰዎች ቤት ተስተናግዷል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከአይሁድ ህግ ጋር የሚቃረኑ ነገሮች ነበሩ። ጴጥሮስም እንደሌሎቹ አይሁዳውያን ወገኖቹ አህዛብን እንደ እርኩስ የሚቆጥር ሰው ነበር።

ለጴጥሮስ አሁን የተመለከተው ራዕይ ግልጽ ሆኖለታል። እርሱ እግዚአብሔር አህዛብን እንደ እርኩስ እንደማይመለከታቸው ተረድቷል። ስለዚህ አህዛብን ሊቀበላቸው ግድ ነው ። ስለዚህ ጴጥሮስም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ያሉ አይሁዳውያን አማኞች በሙሉ ከአህዛብ ወገን የሆኑትን እንደ እርኩስ ላለማየት ይገደዳሉ ማለት ነው። አህዛብም ጭምር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ጥሪ ተደርጎላቸዋል። እግዚአብሄር የጴጥሮስን መረዳት ቀይሮታል፤ ጴጥሮስም ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደተላከ አምኗል። የእግዚአብሔር ትእዛዝም “በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንደሚቀበል” ይመሰክር ዘንድ ነው (ቁጥር 43)። ከዚህ በኋላ የተከሰተው ነገር የእግዚአብሔር ይህንን እውነት በተግባር ማረጋገጥ ነው። ይህንን መልእክት አምነው የሚቀበሉ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታን እንደሚቀበሉ ተነግሮናል። ከጴጥሮስ ጋር ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት የተጓዙ በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአህዛብ ላይ ሲወርድ ተመልክተው በጣም ተደንቀዋል። ከዚያም ጴጥሮስ እነዚህን ሰዎች በኢየሱስ ስም እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ምንም ነገር እንደሌለ ተመለከተ።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 11:1-18 አንብቡ። ለውጥ ሁልጊዜ ተቃውሞን ያስከትላል።

**መልመጃ**:

1. በቁጥር አንድ ላይ የምንማረው የመጀመሪያው ነገር ምንድነው? በይሁዳ ምን አይነት መልእክት ተላለፈ?

   ________________________________________

2. ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ምን ገጠመው (ቁጥር 2)?

   ________________________________________

3. እነዚህ የተገረዙ አማኞችን በሙሉ ያስቆጣቸው ምን ነበር (ቁጥር 3)?

   ________________________________________

4. ከቁጥር 4-17 ያለውን ክፍል አጠቃላይ ሃሳብ አስቀምጡ። ጴጥሮስ የነገራቸው ምን ነበር?

   ________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

5. ጴጥሮስ ያካፈላቸውን የሰሙት አማኞች ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 18)? “ይህን በሰሙ ጊዜም ______________ አሉና። እንኪያስ እግዚአብሔር ______________ ደግሞ ______________ የሚሆን ______________ ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ።”

## ክፍል 3

**ማሰላሰል**

ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ጥሪ ቀና ምላሽ ባይሰጥ ኖሮ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቡ፡

______________________________________________

______________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. እኔስ በግል ህይወቴ ወይንም በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ልለውጠው የሚገባ ልማድ ምንድነው?

______________________________________________

______________________________________________

2. ምህረት በኢየሱስ ክርስቶስ ላመኑ ሁሉ የተሰጠ ነው። እኔስ በግል በህይወቴ ውስጥ ይቅር ልላቸው ወይንም ምህረት ላደርግላቸው የሚገባ ሰዎች ይኖሩ ይሆን?

______________________________________________

______________________________________________

3. ይቅርታ ፍርሃትን ያስወግዳል። ምህረት ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል። ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረኝ ያደርጋል። እግዚአብሔር እኔን ይቅር እንዳለኝ ሌሎችን ይቅር ብላቸው ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል?

______________________________________________

______________________________________________

“እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን” ብለን እንጸልያለን።

4. ምህረት በማድረጋችሁ ምክንያት ይቅር ካላችኋቸው ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነታችሁን በምን መልኩ ተለውጧል?

______________________________________________

**ማሰላሰል**

በጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ ታሪክ ውስጥ የምናገኘው የጥምቀት ስርአት ወደ ኢየሱስ ጽድቅ መጠጋታችንንና ሁላችን አንድ የሆንበትን እውነት ያስታውሰናል፡፡ በምንም ምክንያት ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ቤተሰብነት ውጪ አይሆንም፡፡ ይህ እውነት በገላትያ 3:26-28 በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይህ ክፍል ሁላችንም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ የሆንበትን እውነት ሁልጊዜ እንድናስብ ያደርገናል፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆናችሁበትን እውነት የሚያስታውሳችሁ ነገር ስታገኙ ትኩረት ስጡት፡፡ "በእምነት በኩል __________________ በክርስቶስ ኢየሱስ __________________፤ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፡፡______________ ወይም ______________የለም፥ ______________ ወይም ______________የለም፥ ______________ ______________ የለም፤ ______________ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡"

**ጸሎት**

አምላኬ ሆይ፡ በሌሎች ላይ ስፈርድና ነገሮችን በራሴ መንገድ ስወስን ራሴን አግኝቼዋለሁ፡፡ ሌሎችን ከእኔ አሳንሼ በማየቴ ምክንያት ንሰሃ እገባ ዘንድ ኃጢአቴንም እናዘዝ ዘንድ ይገባኛል፡፡ ሌሎችን ሰዎች ለመውደድ የራሴ የሆነ መሥፈርት አለኝ፡፡ ቀርቤ ችግራቸውን ከመረዳት ይልቅ በእነርሱ ላይ መፍረድን መርጫለሁ፡፡ የመዳንን "ወንጌልን ለሰዎች በመስበክ በሰው ሁሉ ፊት ምሥክርህ እሆን ዘንድ አዝዘኸኛል፡፡ ልቤን አንጻልኝ በድነት የሚገኘውንም ሃሴት በውስጤ አድስ፡፡ ለሰዎች ሁሉ ያሳየኸውን ፍቅር ለሌሎች መንገር እችል ዘንድ ወደዚህ ፍቅርህም ማምጣት እችል ዘንድ እርዳኝ፡፡ ስላበዛህልኝ ጸጋ እና ወደ አንተ ስለሳበኝ ፍቅርህ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**<u>ክፍል 4</u>**

**ትምህርት**

በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሳው ስደት ክርስቲያኖችን በስተ ሰሜን ወዳሉት ሃገራት ማለትም ፊንቄ፣ቆጵሮስ፣እና አንጾኪያ እንዲበተኑ አድርጓቸዋል። ብዙዎች የምስራቹን ቃል ያካፍሉ የነበሩት ለአይሁድ ብቻ ነበር። ሌሎች ደግሞ ለግሪኮች ማለትም ለአህዛብ ይህንን ታላቅ የምሥራች ያካፍሉ ጀመር። በሐዋሪያት ሥራ 11፡12 ላይ እንደተነገረን የእግዚአብሔር እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረች። ብዙ ህዝብም እለት እለት በጌታ ያምኑ ነበር። ይህ ዜና በኢየሩሳሌም ወዳለችው ቤተ ክርስቲያን ሲደርስ በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ወደ አንጾኪያ በርናባስን ላከች። በርናባስም ወደዚያ ስፍራ ሲደርስ የተነገረው ነገር እውነት እንደሆነና የእግዚአብሔር ጸጋም በመካከላቸው ሲሰራ ተመለከተ። በዚህም በጣም ተደሰተ። እርሱም በዚህ እውነት ጸንተው እንዲኖሩ አበረታታቸው።

1. በቁጥር 24 ላይ በርናባስ በምን መልኩ ነበር የቀረበው?

   ሀ.________________________________________

   ለ.__________________________ እና________________

2. በአንጾኪያ ምን እየተከናወነ ነበር (ቁጥር 29)?

   ________________________________________

   ________________________________________

በርናባስም ሳውልን ወደ አንጾኪያ ይዞት በመምጣት በዚያ ብዙ ህዝብ እያስተማሩ አመቱን ሙሉ ቆዩ። በዚያን ጊዜ በአንጾኪያ በጣም ጠቃሚ ነገር ተከናውኗል። በሐዋሪያት ሥራ 11፡26 ላይ ምን ተነግሮናል?

____________________________________________

____________________________________________

**መግቢያ**

በክርስቲያኖች ላይ የተነሳው ስደት አልቆመም። በሐዋሪያት ሥራ 12 ውስጥ እግዚአብሔር ለህዝቡ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን ያደረገውን ድንቅ የማዳን ተአምራት እናነባለን። ይህ ክፍል ስለጴጥሮስ መታሰርና፣ትጸልይ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ስለሰጣት አስደናቂ ምላሽ ይተርክልናል። ይህ ታሪክ በክፉዎች ኢላማ ውስጥ የገቡትን፣የታሰሩትን፣ የተሰደዱትን፣እና ሊገደሉ ያሉትን ሰዎች እግዚአብሔር እንዴት ጣልቃ ገብቶ

እንደሚታደጋቸው ይተርክልናል። ይህ ክፍል በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ወክለው ሌሎች ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡበትን ሁኔታ የሚተርክልን ታሪክ ነው።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 12:1-19 አንብቡ።

**መልመጃ**:

1. ንጉሱ ማን ይባል ነበር (ቁጥር 1)? ______________________________ ምን እያደረገ ነበር (ቁጥር 1)?
   ____________________________________________________________________
2. ንጉሱ በያዕቆብ ላይ ምን አደረገበት (ቁጥር 2)?
   ____________________________________________________________________
3. የአይሁዳውያን ስሜት ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 3)?
   ____________________________________________________________________
4. ሄሮድስ በጴጥሮስ ላይ ምን አደረገበት (ቁጥር 3-4)?
   ____________________________________________________________________
5. ቁጥር 5: "ጴጥሮስም______________________________ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ______________________________ይደረግ ነበር።"
6. ጴጥሮስን ወደ ፍርድ ከማምጣታቸው በፊት ባለው ሌሊት ምን ተከሰተ (ቁጥር 6)?
   ____________________________________________________________________
7. ቀጥሎ የተከናወነውን ነገር እስቲ በራሳችሁ ቃል ግለፁት (ቁጥር 7-10)። ___________
   ____________________________________________________________________
   ____________________________________________________________________
8. በቁጥር 11 ላይ ጴጥሮስ ምን አስተዋለ ? እግዚአብሔር ከምን አዳነው?
   ሀ.________________________________________________________________
   ለ.________________________________________________________________
9. ጴጥሮስ ወደ የት ነበር የሄደው (ቁጥር 12)?
   ____________________________________________________________________
10. በቤቱ ውስጥ የነበሩት እነማን ናቸው? ምንስ እያደረጉ ነበር?
   ____________________________________________________________________
   ____________________________________________________________________

11.ጴጥሮስ በሩን ሲያንኳኳ የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር (ከቁጥር 13-15)?

____________________________________________

____________________________________________

12.በሩን ሲከፍቱ ምን ነበር የተከሰተው? ጴጥሮስን ለማየት ምን ነበር ያደረጉት (ቁጥር 16)?

____________________________________________

____________________________________________

13.ጴጥሮስ ያደረገውና የተናገረው ምን ነበር (ቁጥር 17)?

____________________________________________

14.ከመሄዱ በፊት ምን አይነት መመሪያ ነበር የሰጣቸው (ቁጥር 17)?

____________________________________________

*ማስታወሻ* : ያዕቆብ የኢየሱስ ወንድም ፣የቤተ ክርስቲያን መሪና፣ከቤተ ክርስቲያን አእማዳት አንዱ ነው።

15.እስቲ ለአፍታ ደግሞ ወደ እስር ቤቱ መለስ እንበል.........።በዚያ ምን ተከናወነ (ቁጥር 18)?

____________________________________________

16.ሄሮድስ ምን አደረገ ? ምን አይነት ትዕዛዝ ነበር ያስተላለፈው (ቁጥር 19)?

____________________________________________

## ክፍል 5

### ማሰላሰል

1. *ማንም ይህንን ታሪክ የሚያነብ ሰው በተከሰተው ነገር ፈገግ ማለቱ አይቀርም። እንደሚታወቀው ጴጥሮስ ተንሸራታች ባህሪይ ያለው አይነት ሰው ነበር። ሄሮድስም ጴጥሮስን ይዞ በአስራ ስድስት ወታደሮች መካከል አሰረው። ሌሊቱን በሙሉም እየተፈራረቁ እንዲጠብቁት አደረገ። በዚህ ሁሉ ጥበቃ መካከል ጴጥሮስ በታሰረበት ክፍል ውስጥ በሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ሳለ ብርሃን በዙሪያው አበራ፤ የጌታ መልአክም ጴጥሮስን ጎኑን መትቶ አነቃው። ጴጥሮስን እንዲነሳ አዘዘው በዚያን ጊዜም ሰንሰለቶቹ ከላዩ ላይ ወደቁ። መልአኩም ጴጥሮስ ልብሱን እስኪለብስ ጫማውን እስኪያጠልቅ፣መታጠቂያውን እስኪታጠቅ በቂ ጊዜ ከሰጠው በኋላ እየመራ ከእስር ቤት*

ውስጥ አስወጣው። በጠባቂዎቹ መካከል ተራምደው አለፉ የብረቱ መዝጊያም አውቆ ተከፈተላቸው። በመንገዱ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ መልአኩ ከእርሱ ተለይቶት ሄደ። እናንተ ጴጥሮስን ብትሆኑ ኖሮ ምን እንደተፈጠረ ታስቡ ነበር ? በዚያን ጊዜ ምን አይነት ሃሳብ ወደ ውስጣችሁ ይመጣ ነበር?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

በቁጥር 11 መሰረት ጴጥሮስ ምን እየሆነ እንዳለ ነበር ያስተዋለው? ____________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንደወጣ በመጀመሪያ የሄደው ወዴት ነበር? የዩሐንስ ማርቆስ እናት ማርያም ቤት አማኞች ለጸሎት የሚሰበሰቡበት ስፍራ ነበር ወይንም ቤተ ክርስቲያን ነበር። ሰአቱ እኩለ ሌሊት እንደሆነ እናስባለን ቢሆንም ግን በዚያ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች እየጸለዩ እንደነበረ ተነግሮናል ይሁን እንጂ ጸሎታቸውም መልስ አግኝቷል። ጴጥሮስ በደጅ ቆሟል። ሮዴ የምትባለው አገልጋይ በውጪ የጴጥሮስን ድምጽ ብትሰማም በሩን ከፍታ ግን ልታስገባው አልቻለችም፣ ይልቁኑም በውስጥ ላሉት ልትነግራቸው እየሮጠች ሄደች። ነገር ግን ማንም አላመናትም ነበር። እርሷም መናገሯን አልተወችም ጴጥሮስም ማንኳኳቱን ቀጥሎ ነበር። በመጨረሻም በሩን ከፈቱ፤ እርሱ መሆኑንም አረጋገጡ። በማርያም ቤት ከሚጸልዩት ሰዎች ጋር አብራችሁ ስለጴጥሮስ እየጸለያችሁ እንደሆነ አስቡና ከዚያም በሩን እንዴት ትከፍቱት እንደነበረ አስቡ?______________________________________________________

________________________________________________________________

3. ጴጥሮስ በእስር ቤት ሆኖ ፍርዱን እየተጠባበቀ ነበር። እንደ ሄሮድስ ሃሳብ ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስ ያበቃለት ወይንም የሞተ ሰው ነበር። የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን በመግደል አይሁድን ደስ ስላሰኛቸው፤ አሁን ደግሞ አይሁድን በበለጠ ደስ ለማሰኘት ጴጥሮስን በመያዝ ሊገድለው ፈለገ። የጌታ መልአክ በብርሃን ተገልጦ በእስር ቤት ውስጥ ከመገኘቱ በፊት ጴጥሮስ ልክ በመቃብር ውስጥ እንዳለ ሰው ነበር። ከሞት ወደ ህይወት ነበር የተሻገረው። በጎዳናው ላይ ነጻ እንደወጣ እና እንደተፈታ ሰው ነበር የተመላለሰው። ተሰብስበው ስለእርሱ ይጸልዩ ወደ ነበሩት ሰዎች በመሄድ ጌታ መልአኩን ልኮ እንዴት

እንዳዳነው ተረከላቸው። ጴጥሮስም ከእነርሱ ተለይቶ ከመሄዱ በፊት ለያዕቆብና በኢየሩሳሌም ላሉ ወንድሞች የሆነውን ነገር እንዲነግሩ አሳስቧቸው ነበር። በኢየሱስ ትንሳኤና በጴጥሮስ ከእስር መለቀቅ መካከል ምን ተመሳሳይ ነገር ታገኛላችሁ?

______________________________________________

______________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. ጴጥሮስ በእስር ቤት ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለእርሱ አጥብቆ ጸሎት ይደረግ ነበር (ቁጥር 5)። ስለ አንድ ሰው ለመጸለይ ከሌሎች ጋር ተሰብስባችሁ ታውቃላችሁ? የማይቻል የሚመስለውን ነገር በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ይዛችሁ ቀርባችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ምን አይነት ተአምራት እንዲያደርግላችሁ ጸልያችሁ ታውቃላችሁ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   "እምነትም______________________ስለምናደርገው ነገር________________________ ፥ _________________________ ነገር ___________________ ነው" (ዕብራዊያን 11:1)። እምነት ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊያደርገው የማይችለውን ነገር እንድናምን ያስችለናል።

2. እግዚአብሔር ወደ እርሱ የጸለይነውን ጸሎት እንደሚሰማን ቃል ገብቶልናል። የጸሎት አላማ እኛ የምንፈልገውን ለእግዚአብሔር መንገርና ምላሹን መጠበቅ ነውን? በእርግጥ እንደዚህ አይደለም! ጸሎት ሁልጊዜ ስለ እግዚአብሔር እንድናስብና እንደዚሁም እርሱ ማን እንደሆነ ማሰብ እንድንችል ያደርገናል። ጸሎት እግዚአብሔርን ስለታማኝነቱ ፤የልባችንን መቃተት ሰምቶ እንደ መልካም ፈቃዱና መልካምነቱ ስለመመሱ እንድናመሰግነውና ክብርን እንድንሰጠው ያደርገናል። እግዚአብሔር እንደሚሰማችሁ አምናችሁ እንዳትጸልዩ የሚያደርጋችሁ ምን ነገር አለ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. እግዚአብሔር ጸሎታችሁን እንደናንተ ፈቃድ ሳይሆን እንደ መልካምነቱ እና እንደ በጎ ፈቃዱ እንደሚመልስ ስታስቡ አስቸጋሪ የሚሆንባችሁ ነገር ምንድነው?

4. በተቃራኒው ስንመለከት ደግሞ በማርያም ቤት ተሰብስበው ሲጸልዩ የነበሩት ቅዱሳን እግዚአብሄር ጴጥሮስን ከእስር ቤት አስፈትቶ ወደ እነርሱ በመላክ ጸሎታቸውን እንደሚመልስላቸው አልጠበቁም ነበር፡፡ "አብደሻል"..."በር የሚያንኳኳው መልአኩ ነው" በማለት ነበር ሮዴን የተቃወሟት ፡፡ ሮዴም ከደስታዋ የተነሳ በሩን እንኳን መክፈት አልቻለችም ነበር፡፡ ሌሎቹም የሆነውን ነገር ባለማመናቸው ምክንያት በሩን አልከፈቱም ነበር፡፡

**ጸሎት**:

ወደ እግዚአብሔር ፊት በጸሎት እንድንቀርብ ተጋብዘናል፡፡ አንድ ልጅ በአባቱ ፊት ሆኖ በልቡ ያለውን ሁሉ እንደሚጠይቅ እግዚአብሔርን እንድንጠይቀው ተበረታተናል፡፡ እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ እንደሚወደን ማወቅ አለብን፡፡

# ትምህርት ሁለት

# በመንፈስ ቅዱስ መላክ

## የሐዋሪያት ሥራ 13-14 — የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ

---

**የትምህርት 2 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 2: የሐዋሪያት ሥራ 13-14

መለየትና መላክ

ጳውሎስና ኤልማስ

ጳውሎስ ተወገረ

የጳውሎስ መልእክት

ጢሞቴዎስ

የመቄዶንያው ጥሪ

*መግቢያ*

በመጀመሪያ ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ የገጠመውን ነገር ሰምተናል፡፡ ከዚያ ደግሞ እግዚአብሔር ድነት የተዘጋጀው ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአህዛብም ጭምር እንደሆነ ለጴጥሮስ ራዕይ በማሳየት አስረድቶታል፡፡ እነዚህ እውነታዎች የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ከባድና አጥፊ በሆነ ስደት ውስጥ እንድታልፍ አድርገዋታል፡፡ ያዕቆብ ተገደለ፣ጴጥሮስ ታሰረ፣ጳውሎስና በርናባስ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተጸልዮላቸው ወደ መጀመሪያው የሚሲዮናዊ ጉዞ ተላኩ፡፡

ጳውሎስና በርናባስ ለተሰጣቸው ስራ ባስታጠቃቸው መንፈስ ቅዱስ ነበር የተጠሩት፡፡ ከዚያም በመርከብ ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፡፡ ጳውሎስም ኤልማስ በተባለው ሰው ላይ የፍርድን ቃል ተናገረበት፡፡ እነዚህ ሰዎች የተሰቀለውን ፣የሞተውንና ፣የተነሳውን ክርስቶስን በምን አይነት ግልጥነት፣ መተማመን እና ድርፍረት ይሰብኩት እንደነበር ልብ በሉ፡፡ እውነትን በውሸት ለመለወጥ በሚፈልጉ ባላመኑ ሰዎችን በመካከል የኢየሱስን እውነት በመንገር ለዚህ እውነት እንዲገዙ እና ክርስቶስን እንዲከተሉ ማድረግ ምን ሊመስል እንደሚችሉ አስቡ፡፡ እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ መወገር ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡ?

ጳውሎስና በርናባስ ብርቱ በሆነ ስደትና ሰይፍ መካከል እንኳን አቋማቸውን አለወጡም ነበር፡፡ ኦ ጌታ ሆይ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነትህን በእምንት ይገፍ መገኘት ይሆንልኝ ዘንድ ጸጋህ ያግዘኝ፡፡

## ትምህርት 2

### <u>ክፍል 1</u>

### *መግቢያ*

በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ታሪኮች ቢነገሩም በዚህ ጥናት የምንመለከታቸው ጥቂቶቹን ብቻ ይሆናል፡፡ ከዚህ በፊት የተመለከትናቸው ታሪኮች በአብዛኛው ከጴጥሮስ ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ነገር ግን በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 9 ላይ ሳውል የሚባለውን ጳውሎን እንተዋወቃለን፡፡ ከምዕራፍ አስራ ሶስት ጀምሮ ሚሲዮናዊ ጉዞዎችን በተመለከተ ጳውሎስ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ዋና ትኩረት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የሐዋሪያት ሥራ ጳውሎስ በሄደበት ሁሉ የመንግስቱን ወንጌል ይዞ የሄደባቸውን ሶስት ዋና ዋና ሚሲዮናዊ ጉዞዎች ይዘግብልናል፡፡ ከምዕራፍ 13 እስከ 14 ድረስ ያለው ክፍል የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ጉዞ ታሪክ ይዟል፡፡ የጳውሎስ ህይወት በእነዚህ ጉዞዎች ላይ ምን ይመስል እንደነበር በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 13 እና 14 አንብቡ፡፡ ብዙ ጠልቃችሁ አታስቡ ነገር ግን የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ ታሪክ በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡

**መልመጃ**: የሐዋሪያት ሥራ 13

1. ነቢያትና አስተማሪዎች በቁጥር አንድ ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ የትኛውን ስያሜ በደንብ ታውቁታላችሁ?__________________________እና ______________________________
2. መንፈስ ቅዱስ የሰጠው መመሪያ ምን የሚል ነበር (ቁጥር 2)?

   ________________________________________________________________________
3. እግዚአብሔርን እያመለኩ፣ እየጾሙና ፣እየጸለዩ እንደነበረ ተነግሮናል፡፡ ከዚያ ቀጥለው ምን ነበር ያደረጉት (ቁጥር 3)?

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

   ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ለለያቸው ስራ ይወጡ ዘንድ እጃቸውን ጭነው ጸልየው ሸኟቸው፤ ለአገልግሎቱ ተለዩ፣ ከዚያም ተላኩ!

*ማስታወሻ* : እጅ የመጫን ስርአት ለአንድ አገለግሎት ለተለየ ሰው ቡራኬ የሚሰጥበት ስርአት ነው፡፡ ጳውሎስና በርናባስም እግዚአብሔር ለለያቸው ስራ ወደ ዓለም ሁሉ መልእክትን ይዘው ወጡ!

4. እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ______________________ ወረዱ፤ ከዚያም በመርከብ ______________________ሄዱ፡፡ በዚያ ሲደርሱ ምን ነበር ያደረጉት (ቁጥር 5)?

_______________________________________________

5. የሚረዳቸውና ያገለግላቸው የነበረው ማን ነበር (ቁጥር 5)? ____________________
ስለ ዮሐንስ በሐዋሪያት ሥራ 12:12 ላይ ስለ እርሱ የተጻፈውን አንብቡ፡፡

6. ወደ ጳፉ እንደሄዱ ተነግሮናል፡፡ በጳፉ ምን ሆነ? ምን ነበር የገጠማቸው? የሐዋሪያት ሥራ 6-12 አንብባችሁ ታሪኩን በራሳችሁ መንገድ ግለጹት፡፡

_______________________________________________

_______________________________________________

7. ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር ከጳፉ ተነሥቶ ____________________ ወደምትሆን ወደ ____________________ መጣ፤ (ቁጥር 13)፡፡ በቁጥሩ መጨረሻ ለይ የተነገረን ጥቂት ታሪክ ምንድነው ቁጥር 13?

_______________________________________________

8. ከዚያም በስተሰሜን ወደ ____________________ተጓዙ፡፡ በሰንበት ጳውሎስ በቤተ መቅደስ እንዲያስተምር ጥያቄ ቀረበለት (ቁጥር 14-15)፡፡ ጳውሎስ ለተሰበቡት ሰዎች ያስተላለፈላቸው መልእክት ምን ነበር (ቁጥር 16-41)፡፡ ከቁጥር 38 እስከ 39 ባለው ክፍል ውስጥ ያለው መልእክት ጭብጥ መንድነው? “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ በእርሱ በኩል የ______________________________ እንዲነገርላችሁ፥ በ____________ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ሁሉ ____________በእርሱ ______________ በእናንተ ዘንድ ____________ ይሁን፡፡”

9. ጳውሎስና በርናባስ ምኩራቡን ለቀው ሲወጡ የህዝቡ ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 42-43)?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

10.በቀጣዩ ሰንበት ምን ተከሰተ(ቁጥር 44)?

_______________________________________________

11.አይሁድ በተሰበሰበው ህዝብ ላይ ምን አደረጉ (ቁጥር 45)?

_______________________________________________

12.የጳውሎስና የበርናባስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 46-47)?

_______________________________________________

_______________________________________________

13.የአህዛብስ ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 48)?

_______________________________________________

*ማስታወሻ:* "የተዘጋጁ" የሚለው ቃል ወታደራዊ ቃል ሲሆን ቀጣዩን ግዳጅ የሚወጡ እንደማለት ነው፡፡ ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያ ለአይሁድ ከዚያ ደግሞ በመቀጠል ለአህዛብ ወንጌልን ያደርሱ ጀመር፡፡ በተጨማሪም ሮሜ 1:16-17 አንብቡ፡ "በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ____________ ደግሞም ____________ ሰው፥ ______________የእግዚአብሔር______________ነውና፡፡______________ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ _____________ ወደ ____________ በእርሱ ይገለጣልና፡፡" (ቁጥር 16)፡፡

14.በሐዋሪያት ሥራ 13:49 በሁሉም ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል__________________ እንደሆነ ተነግሮናል፡፡ በቁጥር 50-51 ጳውሎስና በርናባስ ምን ገጠማቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

15.ቁጥር 52: "እነርሱ ግን ______________አራግፈውባቸው ወደ ______________ መጡ፡፡ በደቀ መዛሙርትም ______________ና ______________ሞላባቸው፡፡"

**ማሰላሰል**:

ጳውሎስ በጳፉ በነበረበት ጊዜ ኤልማስ ከሚባለው ጠንቋይ ጋር ተገናኝቶ ነበር፡፡ ከቁጥር 9-11 ባለው ክፍል ጳውሎስ በኤልማስ ድርጊት በመቆጣቱ ጠንቋዩን ኤልማስን "የዲያብሎስ ልጅ፣ የጽድቅ ጠላት በማለት…" ጠርቶታል፡፡ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ኤልማስን "ክፋት ሁሉ የሞላበት አሳች" እንደሆነ አድርጎ ነው ያስቀመጠው፡፡ በመጨረሻም ጳውሎስ "የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን?" በማለት ተናገረው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ትኩር ብሎ ኤልማስን ተመለከተው፡፡ እስቲ ይህንን ሁኔታ ጌታ "ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን

ታሳድደኛለህ?” ከሚለው የኢየሱስ ንግግር ጋር አነጻፅሩት። ጳውሎስ ኤልማስን እንደዚህ አለው “አሁንም፥ እነሆ፥ ____________________በአንተ ላይ ናት፥ ____________________ ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ____________________አለው።” (ቁጥር 11) ጳውሎስ ይህንን ሰው ያስተናገደው ልክ እርሱን ጌታ በተገናኘበት መንገድ ነበር። ኤልማስ እውር እንደሚሆን ነገረው። “ያን ጊዜም ______________ወደቀበት፥ በእጁም ______________ እየዞረ ፈለገ። በተጨማሪም የሐዋሪያት ሥራ 9:8 ተመልከቱ።

<u>**ክፍል 2**</u>

***መግቢያ***:

እስቲ ለጥቂት ጊዜ መለስ ብለን ጌታ ሐናንያን ወደ ሳኦል ሄዶ እጁን ጭኖ እንዲጸልይለት ምን ብሎ እንደነገረው እናስብ (የሐዋሪያት ሥራ 9:10-12)። በሐዋሪያት ሥራ 9:16 ጌታ እንደዚህ አለ “________________________ስንት________________________ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና አለው። ቀጣዩ ምዕራፍ ጳውሎስ ስለ ጌታ ስም ምን አይነት መከራዎችን በጽናት እንደተጋፈጠ ይነግረናል።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 14 አንብቡ።

***መልመጃ***:

1. ጳውሎስና በርናባስ አንጾኪያን ትተው ከ120- 160 ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ ወዳለችው ኢቆንዮን ሄዱ። ከዚህ በፊት እንደሚያደርጉት ወደ አይሁድ ምኩራብ ሄዱ። ሰዎቹ ለመልእክቱ ስለሰጡት ምላሽ ምንድነው ተነገረን። (ቁጥር 1)?

   ________________________________________________

2. ያላመኑት አይሁድ ምን ነበር ያደረጉት (ቁጥር 2)?

   ________________________________________________

3. ጳውሎስና በርናባስ ከጌታ ጋር የነበራቸውን ጥምረት ልብ በሉ (ቁጥር 3)።

   ሀ. የጳውሎስና የበርናባስ ኃላፊነት ምን ነበር?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

   ለ. የጌታስ ድርሻ ምን ነበር?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

4. ህዝቡ ተከፋፍሎ ነበር። በአህዛብና በአይሁድ ታቅዶ የነበረው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 5)?

___________________________________________________________________

5. ነገር ግን እቅዳቸው ከሸፎ ደቀ መዛሙርቱ ወደ______________________ እና ____________________ተበተኑ።ከዚያም ወደ______________________ቀጠሉ።

6. በልስጥራን አስደሳች ታሪክ ተከናውኗል። በታሪኩ የመጀመሪያ ክፍል ምን ተከናወነ (ከቁጥር 8-10)?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

7. ሽባው ሰው በመፈወሱ የህዝቡ ምላሽ ምን ይመስል ነበር? እስቲ ከቁጥር 11-18 ያለውን ሁኔታ ግለጹ።

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

**ትምህርት**

የህዝቡ ምላሽ አማልእክቶቻቸው ሰው ሆነው በመካከላቸው እንደተገኙ በማሰብ ለአማልክቶቻቸው ያዘጋጇቸውን ኮርማዎች መሰዋት ነበር። ይሁን እንጂ ነገሮች ወዲያውኑ ነበር የተለወጡት። የጳውሎስ የጉዞ ስፍራ ከነበሩት ሁለቱ ስፍራዎች ማለትም ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን የሆኑ አንዳንድ አይሁዶች ደቀ መዛሙርቱን ተከትለው ልስጥራ ድረስ ህዝቡን ለማሳመጽ መጡ። ቁጥር 19 ላይ እንደተነገረን እንዳሰቡትም ህዝቡን ማሳመጽ ችለው ነበር (ቁጥር 19)። ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ____________ የሞተም መስሎአቸው ________________ ወደ __________ጐተቱት።

**መልመጃ**:

1. ሰዎቹ ጳውሎስ የሞተ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን ቁጥር 20 ስለዚህ ሁኔታ ምን ይነግረናል?

___________________________________________________________________

ጳውሎስ አለመሞቱ ብቻ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ በዙሪያው ከበውት ሳሉ "ተነስቶ _______________________________________________________________::"

2. በበነጋውም እርሱና በርናባስ ከተማይቱን ለቀው ወደ ____________________ሄዱ (ቁጥር 20)

3. የደርቤን ሰዎች ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 21)?

_______________________________________________

4. ለምን ይሆን ወደ ልስጥራን፣ኢቆንዮን እና አንጾኪያ የተመለሱት?

_______________________________________________

5. በቁጥር 22 ላይ የጳውሎስ ቃል ምን የሚል ነበር?

"ወደ______________________ ______________________እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ" በቁጥር 23 መሰረት ጳውሎስና በርናባስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያደረጉት ሌላው ነገር ምን ነበር ?

_______________________________________________

_______________________________________________

6. ከዚያም ደቀመዛሙርቱ ______________________ለ______________________ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ሄዱ (ቁጥር 26)፡፡

7. አንጾኪያ ሲደርሱ ምን አደረጉ (ቁጥር 27)?

ሀ.______________________________________________

ለ.__________________________________ እና __________

_______________________________________________

**<u>ክፍል 3</u>**

***ገለጻና ከህይወት ጋር ማዛመድ***:

1. የጳውሎስና የበርናባስን የመጀመሪያ ሚስዮናዊ ጉዞ ስንመለከት የእነዚህን የእምነት ሰዎች ብርታት ስንመለከት በጣም ያስገርማል፡፡ በአንጾኪያ የተሰበከው መልእክት "በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአት ስርየት ታውጆላችኋል" የሚል ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህንን እውነት ህዝቡ ይሰማ ዘንድ በቀጣዩ እሁድ እንዲናገሩ ብርታት አግኝተዋል፡፡ አይሁዶቹ በቅናት ተነሳስተው የጳውሎስን ትምህርት የሚቃወም ንግግር ይናገሩ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ስደት ተነሳ ደቀ መዛሙርቱም ከዚያ አካባቢ ተሰደዱ፡፡

ሀ. ጥያቄ: እናንተስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአት ስርየት ያገኛችሁ ሰዎች ናችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳጸደቃችሁና በእግዚብሔር ፊት ጻድቅ ሆናችሁ እንደተቆጠራችሁ ያወቃችሁ ሰዎች ናችሁ? እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ለ. ጥያቄ: ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ስትመሰክሩ ሌሎች ከእናንተ ተቃራኒ ሆነው ተናግረው ወይንም ተቃውመዋችሁ ያውቃሉ? ተቃውመዋችሁ የሚያውቁ ከሆነ ተቃውሟቸውን የገለጡት ምን በመናገርና በማድረግ ነበር?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. የጳውሎስን አካላዊ ስደት ሳንመለከት ይህንን ምዕራፍ መደምደም አግባብ አይሆንም፡፡ ጳውሎስ በዚህ ከተማ በድንጋይ ተወግሮ እንደሞተ ተቆጥሮ ከከተማው ውጪ ተጎትቶ ተጥሎ ነበር፡፡ እነዚህ ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን የመጡ አይሁዶች ህዝቡን ምን ብለው ለአመጽ እንዳሳመኑት ስናስብ ሊያስገርመን ይችላል፡፡ ከጥቂት ሰአታት በፊት እንደ አማልክት የቆጠሯቸውን ሰዎች ወዲያው ፊታቸውን አዙረው በድንጋይ እንዲወግሯቸው ያደረጓቸው ምን ብለው ቢያሳምኗቸው ይሆን ? የእነዚህን ሰዎች ወደ ልስጥራን የመመለስ ድፍረት ስንመለከት ለመግለጽ እንኳን ያስቸግረናል፡፡ የእነዚህ አማኞች በልስጥራን መገኘት ለአዲሶቹ አማኞች ምን ማለት ይመስላችኋል? ስደቱ በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ብቻ ነው? የሚል ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባናል፡፡ ኢየሱስ ሳውልን በደማስቆ መንገድ ላይ ምን ነበር የጠየቀው (የሐዋሪያት ሥራ 9:4)? “ሳውል ሳውል ስለምን ______________________________?”

3. ወደ ልስጥራን መሄድ ብቻ ሳይሆን ወደ ተላኩበት ወደ አንጾኪያ ተመልሰው ደቀ መዛሙርቱን ጎብኝተው፣ በእውነተኛው እምነታቸው እንዲጸኑና እንዲጠነክሩ አበረታተዋቸው ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን መረጡላቸው፡፡ እንዴት ነበር ይህንን ያደረጉት? ከየት ነበር ይህንን ሁሉ ብርታት ያገኙት? በእምነታቸው ጠንክረው እንዲጓዙ ያደረጋቸው ምን ነበር? በሐዋሪያት ሥራ 13:2 መሰረት መንፈስ ቅዱስ ለጠራቸው ስራ እንደለያቸው ተምረናል፡፡ ከዚህ ምን እንረዳለን? እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4. እስቲ እራሳችሁን ጠይቁ: በስሙ በማመኔ ልጁ ባደረገኝ በእግዚአብሔር እንደተላኩ አምናለሁ? ለእግዚአብሔር የጽድቅ አላማ መለየቴን በምን መንገድ ነው በህይወቴ እያንጸባረኩ ያለሁት?

________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________

**በጥልቀት መመልከት**:

በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:10 ጳውሎስ በአንጾኪያ፣ በኢቆንዮን፣በልስጥራን የነበረውን ልምምድ ወደ ኂላ ተመልሶ እያስታወሰ ለጢሞቴዎስ ይነግረዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በደንብ እንደሚያውቀውና የቅርቡ ሰው እንደሆነ ያስታውሰዋል። እስቲ ይህንን ክፍል ጻፉት:

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

ከዚያም ቀጥሎ እንደዚህ ብሎ መናገሩን ቀጠለ: "ጌታም____________________________ አዳነኝ።" አዳነኝ የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ "ሯማይ" የሚል ሲሆን ትርጉሙም ከአንድ አደጋ ውስጥ ነጥቆ ማውጣት የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔርም በእርግጥ ያደረገው እንደዚያው ነበር። አይመስላችሁም? ጳውሎስ በዚህ ክፍል ጢሞቴዎስንም ሆነ እኛን ስደትና መከራ ሲደርስብን ብዙም እንዳይደንቀን በማበረታታት ይመክረናል። ልክ እርሱን ከመከራ ውስጥ ነጥቆ እንዳወጣው ሁሉ እኛንም ነጥቆ እንደሚያወጣን ያሳስበናል።

**ጸሎት**:

በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ እንደሚሰደዱ እውነታውን ልንረዳ እንደሚገባ ያስረዳናል (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12)። እግዚአብሔር ወደ እራሱ እንዲያስጠጋችሁ የልባችሁንም ሃሳብ ለእርሱ ግልጥ እንዲሆን ፍቀዱለት።

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

**<u>ክፍል 4</u>**

**በጣም ጠቃሚ ትምህርት**:

የሐዋሪያት ሥራ 15:1-35 ስለ ወደፊቱ ክርስትና ወሳኝ የሆነ ትምህርት የያዘ ክፍል ነው፡፡ ምናልባት የግርዘት ጉዳይ ለእናንተ እንግዳ ነገር ሊሆን ይችላል፣በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ግርዘትን በተመለከተ የተደረገው ውሳኔ ክርስትና የአይሁድ እምነት ንኡስ ክፍል ሳይሆን ራሱን የቻለ አዲስ የዓለም እምነት እንደሆነ ያስረዳናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ውሳኔ አንድ ሰው የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን በመጀመሪያ መገረዝ አለበት የሚል ቢሆን ኖሮ አንድ ሰው ኢየሱስን ለመከተል በመጀመሪያ የአይሁድ እምነት ተከታይ መሆን አለበት የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው አይሁዳዊ ለመሆን በመጀመሪያ የሚያደርገው የግርዘት ስርአትን መፈጸም ነው፡፡ አንድ ሰው በክርስቶስ ህይወት ለመኖር ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ ሊኖር እንደማይገባው የሚደነግገው ቃል ያለው በዮሐንስ 14:6፤ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡" የእግዚአብሔር ልጆች የሆነው ህግን በመጠበቅ፣ወይንም በመገረዝ፣ወይንም ሌላ አይነት ስርአት ፈጽመን ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፡፡

**መግቢያ**:

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊው ጉዞአቸው ወደ ተመሰረቱት አብያተ ክርስቲያናት ተመልሰው ለመሄድ ፈለጉ፡፡ ነገር ግን በጵንፍልያ ትቷቸው የሄደውን ዮሐንስ ማርቆስን ይዞ በመሄድና ባለመሄድ ላይ ጠንከር ያለ አለመስማማት ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት በመካከላቸው መለያየት ሆነ፡፡ በርናባስ ዮሐንስ ማርቆስን ይዞ ወደ ቆጵሮስ እንደተጓዘ ተነግሮናል፡፡ ጳውሎስ ደግሞ ከሲላስ ጋር አብያተ ክርስቲያናትን እያበረታቱ በስተ ሰሜን ተጓዙ፡፡ (የሐዋሪያት ሥራ 15:36-41)፡፡"

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 16:1-10 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ______________________እንዳገኘ እናነባለን፡፡ ይህ ወጣት በ______________________________ ደቀ መዝሙር ነበር፡፡ ጳውሎስና ጢሞቴዎስን ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲዘዋወሩ አገኛቸው፡፡

2. በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 5)?

ሀ.______________________________________________________________

ለ.______________________________________________________________

3. ጳውሎስና ባልንጀሮቹ በጉዞ ላይ ሳሉ ቀጥለው ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የጌታ መንፈስ በመራቸው አቅጣጫ ይጓዙ ነበር (ቁጥር 6-7)፡፡

_____________________ወደ ምትባለው ከተማ ተጓዙ (ቁጥር 8)፡፡

4. በቁጥር 9 መሰረት ምን ተከሰተ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

5. ጢሮአዳን ትተው ወደ____________________________አቀኑ (ቁጥር 10)፡፡ አብረው የነበሩት ምን ወደሚለው ድምዳሜ ደረሱ (ቁጥር 10)?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ገለጻ**:

ጳውሎስ ባገኘበት ስፍራ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ለመስበክ ይጓጓ ነበር፡፡ ነገር ግን የሚጓዘው የጌታ መንፈስ ወደመራው ብቻ ነበር፡፡ በእርግጥ ጳውሎስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት ይነጋገር እንደነበረ አብረውት የነበሩትም ወዴት መሄድ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው እንዴት ይወስኑ እንደነበር አናውቅም፡፡ እንዳይሄዱ የጌታ መንፈስ ከለከላቸው፣ወደዚያ እንዳይሄዱ የጌታ መንፈስ ነገራቸው የሚል ቃል ነው ተጽፎ የምናገኘው እንጂ በምን አይነት መንገድ እንደነገራቸው አልተጻፈልንም፡፡ ጉዞአቸውን የሚያደረጉት በእግር እንደመሆኑ መጠን እነዚህ የወንጌል መልእክተኞች የሚገጥማቸውን ጭንቀት መገመት አይከብደንም፡፡ ከዚያ ደግሞ የመቄዶንያው ሰው ህልም ተከሰተ፡፡ በዚያ ህልም  የተላለፈው መልእክት ቀላል ነበር "ወደ መቄዶንያ መጥተህ እርዳን" የሚል ነበር፡፡ ጳውሎስ ያየውን ህልም ለጓደኞቹ አካፈላቸው ከዚያም ሁሉም በፍጥነት  ከጳውሎስ ጋር ለመሄድ ተዘጋጁ፡፡ የደረሱበት ድምዳሜ ወደዚያ ስፍራ ወንጌል እንድናደርስ እግዚአብሔር ፈልጓል የሚል ነበር፡፡

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

ምናልባት በህይወታችን ራዕይ ወይንም ህልም የማየት ልምምድ አይኖረንም ይሆናል ቢሆንም ይህ ክፍል በጣም ጠቃሚና ወሳኝ ነገር ያስተምረናል፡፡ ጳውሎስ በአገለግሎቱ

በእርግጥም የእግዚአብሔር ሰው ነበር፡፡ አንድ ሰው አምኖም፤ ተጠምቆም በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውስጥ እንደሚኖር ጳውሎስ የእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም የጳውሎስ አምላክ ሆኖ ለመገለጥ ፈቅዶ ነበር፡፡ "እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፡፡" (ኤርምያስ 32:38 እና 2 ቆሮንቶስ 6:16)፡፡ ይህ እውነት ለእኔና ለእናንተም ይሰራል፡፡ በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡9 "እናንተ ግን ________________ ወደ________________የጠራችሁን ________________ እንድትናገሩ ________________ ትውልድ፥ የንጉሥ ________________፥ ________________፥ ለርስቱ ________________ናችሁ፤" እኔና እናንተም ልክ እንደ ጳውሎስ ጨለማው ተወደግዶ የእግዚአብሔር ብርሃን በሰዎች ሁሉ ህይወት ይበራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ክብር ለሰዎች ሁሉ ልናውጅ ተጠርተናል፡፡

ስለዚህ ጥያቄ ሊሆን የሚባው ...እኔም እንደ ጳውሎስ አገልጋይ ሆኜ ከተጠራሁ አገልግሎቴ ምንድነው ? እግዚአብሔር እኔን የት ነው ያስቀመጠኝ? ማንን ነው እንዳገለግል የተጠራሁት? ከእኔ ጋር እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር የሰጠኝ ሰዎች እነማን ናቸው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

የጳውሎስ አገለግሎት ከእኔና ከእናንተ የተለየ ነው፡፡ ሁሉም ሰው የራሱን የሆነ ከእግዚአብሔር የተሰጠው አገልግሎት አለው፡፡ ልክ ጳውሎስ በራዕይ እንደተመለከታቸው በመቄዶንያ እንዳሉት ሰዎች እኛም ልንሄድበት የሚገባን መቄዶንያ ሆነው የሚጠሩን ልናገለግላቸው የሚገባን ሰዎች አሉ፡፡ ልክ ጳውሎስን እንደጠራው እግዚአብሔር የምስራቹን ለሰዎች ሁሉ እንናገር ዘንድ ጠርቶናል፡፡ ጳውሎስ እንደደረሰበት ድምዳሜ እኛንም እግዚአብሔር ወንጌልን እንሰብክ ዘንድ ጠርቶናል ወደሚል ድምዳሜ መድረስ አለብን፡፡ እርሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል እኛ ደግሞ ወደ ሰዎች ስንሄድ እርሱን ይዘን ወደ ሰዎች ሁሉ እንሄዳለን፡፡

**ጠንከር ያለ ጥያቄ፡**

ጌታን እንደሚያገለግል እንደ አንድ ወንድ ወይንም ሴት ከባሌ ጋር ወይንም ከሚስቴ ጋር የሚኖረኝ ግንኙነት እና አጠቃላይ የትዳር ህይወቴ ላይ አገለግሎቴ ሊፈጥር የሚችለው ልዩነት ምንድነው? ከልጆቼ ጋር ፣ከእህቴና ከወንድሜ ልጆች ጋር? ከስራ ባልደረቦቼ

ጋር፣ከአሰሪዬ ጋር?  አብረውኝ ከሚማሩት ጋር፣ከሚያስተምሩት በአጠቃላይ በዙሪያዬ ካሉት ሰዎች ጋር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?

## የሐዋሪያት ሥራ 16-19 — ሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ

---

**የትምህርት 3 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 3፡ የሐዋሪያት ሥራ 16-19

- ጳውሎስና ልድያ
- ጳውሎስና የእስር ቤቱ ሃላፊ
- ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች
- ጉዞው ቀጠለ
- ቤተ ክርስቲያንን ማጠናከርና ማስፋፋት

*መግቢያ*

ስደቱ በበረታ ቁጥር ቤተ ክርስቲያን እየሰፋች መጣች፡፡ ጳውሎስና ሲላስ ከተጓዟቸው ሶስት ሚሲዮናዊ ጉዞዎች ሁለተኛው፡፡ በተጓዙበት ሁሉ ተጽኖአቸው እየጨመረ ድንበራቸውም እየሰፋ መጣ፡፡ እግረ መንገዳቸውንም በምኩራቦችና ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ስፍራዎች ሁሉ መስበክ ቀጠሉ፡፡ እስቲ አሁንም ይህንን አስደሳች ጉዞ አብረን እንጓዝ፡፡ እግዚአብሔር የልድያን፣የወህኒ ቤት ጠባቂውን እንደዚሁም የገዢውን ልብ ሲከፍት እያያችሁ ሃሴት አድርጉ፡፡ ልክ እንደነ ጳውሎስም የትኛው የህይወታችሁ ክፍል ለወንጌል በሰዎች ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርግ ተመልከቱ፡፡

ሰዎች ወንጌል ሲሰበኩ የተለያዩ ምላሾች አሏቸው፡፡ አንዳንዶች መልእክቱን ሰምተው ይቀበሉታል፣ አንዳንዶች ደግሞ ሰምተው ብዙም ስፍራ አይሰጡትም፣አንዳንዶች ደግሞ ሰምተው እንዳልሰማ ይሆናሉ፣ ሌሎች ደግሞ ጭራሹኑ ለወንጌል ጠላቶች ሆነው ይነሳሉ፡፡ ነገር ግን የሰዎች ምላሽ ምንም ይሁን ምን ጳውሎስና ሲላስ በእምነታቸው ጸንተው ወንጌልን በመስበክ እስከመጨረሻው ጸንተው ነበር፡፡

እነኚህ ሰዎች ላለፉበትና ለማይቀረው ስደት ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡ ለመሆኑ ጳውሎስ ለመከራ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል ? በእስር ቤት ውስጥ ምን እንዳደረገ ተመልከቱ፡፡ እነዚህ ሚሲዮናውያን ስለወንጌል የሚገጥማቸው ስደትና መከራ ምንም አይነት ፍርሃት አይፈጥርባቸውም፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ሚሲዮናውያን ጋር መከራን ተቀበሉ፤ ከህይወታቸውም ትምህርት ውሰዱ፡፡ አስቸጋሪ በሆነ ስፍራ መዝሙር ሲዘምሩ ተመልከቷቸውና እንደዚህ ብላችሁ እራሳችሁን ጠይቁ “እኔስ በዚህ ሁኔታ ውስጥ መዘመር እችል ይሆን ?”

## ትምህርት 3

**<u>ክፍል 1</u>**

***መግቢያ***: የጳውሎስ ጉዞ ቀጥሏል…

**የቤት ስራ**: የሐዋሪያት *ሥራ* 16:11-15 አንብቡ

***መልመጃ***:

1. በመጀመሪያ ወደ ___________________________ተጓዙ፡፡ መቄዶንያ እንደ ገላትያ የአንድ ከተማ ስም መጠሪያ አይደለም፡፡ መቄዶንያ የአንድ አካባቢ መጠሪያ ሲሆን ፊልጵስዮስ፣ተሰሎንቄ፣እና ቤሪያን የመሳሰሉ ከተሞችን በውስጡ ይዟል፡፡ ስለ ፊልጵስዮስ ምን የተነገረን ነገር አለ (ቁጥር 12)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

   ፊልጵስዮስ ጡረታ የወጡ የሮም ወታደሮች የሚኖሩባት ከተማ ነች፡፡ በዚች ከተማ ብዙ አይሁዳውያን አይኖሩባትም፡፡ ምኩራብ ለመመስረት የሚበቃ የአይሁድ ቁጥር ስለሌለ የጸሎት ስፍራ በከተማይቱ ዳርቻ ላይ በሚገኝ ወንዝ አካባቢ ነው ያለው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስና ሲላስ እንደተለመደው አማኞችን ለማግኘት ወደዚህ ስፍራ ነበር የሚሄዱት፡፡

   *ማስታወሻ* : አንድን ምኩራብ ለመመስረት ቢያንስ አስር አይሁዳውያን መኖር አለባቸው፡፡

2. ጳውሎስና ሲላስን ስታደምጥ የነበረቸው ሴት ማን ትባላላች (ቁጥር 14)?___________ ስለ እርሷ ምን እንማራለን?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. ለሰማችው መልእክት እንድትታዘዝ ጌታ ልቧን ከፈተላት፡፡ ልድያ በምን አይነት መንገድ ነበር ምላሽ የተጠቸው (ቁጥር 15)?

   ሀ.___________________________________________________________

   ለ.___________________________________________________________

4. ጳውሎስ ለግብዣዋ የሰጠው ምላሽ ምን ይመስል ነበር? እነዚህን በመንገድ ብዛት የደከሙ፣የተራቡ፣ የዛሉ ሰዎች ቤት ውስጥ ገብተው እንዲያርፉ ማስገደደስ ከባድ ይመስላችኋል?

______________________________________________

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት *ሥራ* 16:16-40 አንብቡ

***መልመጃ***:

1. ጳውሎስና ሲላስ ወደ ጸሎት ሲሄዱ በመንገዳቸው ላይ ማንን ነበር ያገኙት (ቁጥር 16-17)? ስለ እርሷ ምን ተነግሮናል?

______________________________________________

______________________________________________

2. በቁጥር 18 ላይ ምን ሆነ?

______________________________________________

______________________________________________

*ማስታወሻ* : አዲስ ኪዳን የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ "ተቸገረ" የሚለውን ቃል "ዲያፖኒዎ" በሚል ቃል የሚገልፀው ሲሆን ትርጉሙም "ደከመ"፣ "በአንድ ተደጋጋሚ ድርጊት ታከተ" የሚል ነው።

3. ብላቴናይቱን የያዛት መንፈስ ለቋት ሄደ (ቁጥር 18)። ምን አይነት የተያያዘ ሁኔታ ነው የተከሰተው!

   ሀ. የብላቴናይቱ ባለቤቶች ምን አደረጉ (ቁጥር 19) ?

   ______________________________________________

   ለ. ለከተማው ገዢ ምን ብለው ነገሩት ?

   ______________________________________________

   ሐ. የህዝቡስ ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 22)?

   ______________________________________________

   መ. የከተማው ገዢ ምን አይነት ትእዛዝ አስተላለፈ?

   ______________________________________________

   ሠ. ከዚህ የተነሳ ጳውሎስና ሲላስ ምን አይነት ችግር ገጠማቸው?

   ______________________________________________

ረ. የእስር ቤቱ ጠባቂ ምን እንዲያደርግ ትእዛዝ ተሰጠው (ቁጥር 23)?

______________________________________________

ሰ.የእስር ቤቱ ጠባቂስ ምን አደረገ?

______________________________________________

4. የብላቴናይቱ ባለቤቶች፣ የከተማው ገዢ፣ህዝቡ እና የእስር ቤቱ ጠባቂ ጳውሎስና ሲላስን ለማጥቃት የየራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል። በመጨረሻ ነገሩ በረደ። እንደገና እግዚአብሔር ለባሮቹ ተነሳ። ጊዜው እኩለ ሌሊት ነበር በዚያን ሰዓት ጳውሎስና ሲላስ ምን እያደረጉ ነበር (ቁጥር 25)?

______________________________________________

______________________________________________

5. በቁጥር 26 ላይ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

______________________________________________

______________________________________________

6. የእስር ቤቱ ጠባቂ ምን ነበር ያደረገው (ቁጥር 27)?

______________________________________________

______________________________________________

7. ጳውሎስ ምን ብሎ ነበር የጮኸው (ቁጥር 28)?

______________________________________________

8. የእስር ቤቱ ጠባቂ ምን ነበር ያደረገው? ጳውሎስና ሲላስን ምን ብሎ ነበር የጠየቃቸው (ቁጥር 29-30)?

______________________________________________

______________________________________________

9. እነርሱም እንደዚህ በማለት ምላሽ ሰጡት

"______________________________________________።"

10. ጳውሎስና ሲላስ የጌታን ቃል ለሁሉም ነገሯቸው። ከዚያስ ምን ሆነ (ቁጥር 33-34)?

ሀ.______________________________________________

ለ.______________________________________________

11. በቁጥር 34 ላይ ስለ እስር ቤት ጠባቂው የተነገረን ምንድነው?

12. ታሪኩስ በምን ተደመደመ? በከተማው ገዢ የተላለፈው መልእክት ምን የሚል ነበር (ነበር 35)?

13. ከእስር ቤቱ ጠባቂ ለተላለፈው ትእዛዝ የጳውሎስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 37)?

14. የጳውሎስ ጥያቄ ምን ነበር (ቁጥር 37)?

15. ለጳውሎስ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 38-39)?

ሀ. ሎሌዎቹም ______________________________

ለ. መጥተውም ______________________________

ሐ. አውጥተውም __________________ ለመኗቸው

16. ጳውሎስና ሲላስ ወዴት ነበር የሔዱት (ቁጥር 40)?

17. በዚያ ምን አደረጉ?

## <u>ክፍል 2</u>

**ማሰላሰል** :

1. በልድያ እና በእስር ቤት ጠባቂው መካከል ያለው ንጽጽር እንዴት የሚደንቅ ነው! ጳውሎስና ሲላስ በልድያም ቤት ሆነ በእስር ቤት ጠባቂው ቤት በቃልም ሆነ በመዝሙር የሰበኩት ኢየሱስን ነው፡፡ በእስር ቤት ውስጥ እግዚአብሔርን በዝማሬ እያመለኩ እንደነበረ ተነግሮናል፡፡ ልድያም ይህንን ነገር ትሰማ ነበር፡፡ የእስር ቤቱም ጠባቂም ይህንን ሰምቷል፡፡ ጳውሎስና ሲላስ የተፈጠረውን ሁኔታ ስለ ኢየሱስ ለመመስከር ተጠቀሙበት፡፡ እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ:

2. ጳውሎስና ሲላስን ወደ ገበያው ስፍራ ተጎትተው ሲወሰዱ በጢሞቴዎስና በሉቃስ አእምሮ ምን የሚመላለስ ይመስላችኋል? ቀጣዮቹ እነርሱ እንደሆኑ አስበው ይሆን ? ጳውሎስና ሲላስን ድጋሚ በህይወት እንደሚያይዋቸው አስበው ይሆን? እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን ሃሳብ:

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ህዝቡ ሲጎትታቸው፣ ሲያንገላታቸው ፣ ሲደበድቧቸው፣ ሲሰድቧቸው፣ ወደ እስር ቤት ሲወስዷቸው፣ በውስጠኛው እስር ቤት ውስጥ ሲጥሏቸው፣በሰንሰለት ሲያስሯቸው በሲላስ አእምሮ ውስጥ ምን እየተመላለሰ የነበረ ይመስላችኋል? እኛ እስክናውቅ ድረስ ሲላስ በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳላለፈ እናስባለን። ምን አይነት ስቃይ ነው! ስለወንጌል እንዴት ያለ ከባድ ዋጋ ነው የከፈሉት! ጳውሎስ በአንጾኪያ ላሉት ደቀ መዛሙርት ያስተላለፈውን ቃል መለስ ብላችሁ አስታውሱ (የሐዋሪያት ሥራ 14:22) እና ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12)። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ:

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

4. ልድያና የእስር ቤቱ ጠባቂ ተጽእኖ መፍጠር የሚችሉ ሰዎች ናቸው። ልድያ ከቤተሰቦቿ ጋር አምና እንደተጠመቀች ተነግሮናል (የሐዋሪያት ስራ 16:15)። ከዚህም በተጨማሪ የእስር ቤቱ ጠባቂ ከመላው ቤተሰቡ ጋር አምኖ እንደተጠመቀ ተነግሮናል (የሐዋሪያት ሥራ 16:33)። በቁጥር 34 ላይ የእስር ቤቱ ጠባቂ እርሱና ቤተሰቡ በማመናቸው ምክንያት የእስር ቤቱ ጠባቂ በደስታ እንደተሞላ ተነግሮናል። የእነዚህ ሰዎች የህይወት ተጽእኖ ብዙ ሰዎችን ወደ ዘላለም ህይወት እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን አስተያየት ግለጹ፡

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

ለዘላለም ህይወት በሌሎች ላይ ተጽእኖ ማድረግ የምትችሉ ሰዎች አድርጋችሁ እራሳችሁን አስቡ፡፡ ይህንን ጉዳይ ብታውቁትም ባታውቁትም በሌሎች ላይ ተጽእኖ ማድረግ የምትችሉ ሰዎች ናችሁ፡፡ ሰዎች የእናንተን ህይወት ይመለከታሉ፤ለህይወት የምትሰጡትን ምላሽ፣ለሚገጥማችሁ ችግር የምትሰጡትን ምላሽ፣በአጠቃላይ እንዴት እንደምትኖሩ ሌሎች እናንተን ይመለከታሉ፡፡ ኢየሱስን እንደሚያውቅ ሰው ሌሎች እንዴት እየኖራችሁ እንዳለ ይመለከቷችኋል፡፡

1. በእናንተ ዙሪያ ያሉ እናንተ በጎ ተጽእኖ ልታደርጉባቸው የሚገባቸው ሰዎች እነማን ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

2. ታዲያ በሰዎች ህይወት ላይ ተጽእኖን እንደሚፈጥር ሰው ህይወታችሁን በምን አይነት መንገድ እየኖራችሁት ነው ?

______________________________________________

______________________________________________

3. ብዙ ሰዎች በጎ ተጽእኖ ሊያደርጉባቸው የሚችሉ ብዙ ልጆች በዙሪያቸው አሏቸው፡፡ ልጆቻችሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ህይወት ይኖራቸው ዘንድ እንዴት ነው ተጽእኖ የምታደርጉባቸው?

______________________________________________

______________________________________________

**ጸሎት**:

የዘላለም ህይወት አግኝታችሁ እርሱን ለማገልገል እድል ስለሰጣችሁ ጌታን አመስግኑት፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች በክርስቶስ ወዳለው እውነት ለማምጣት ተጽእኖ ፈጣሪዎች ያደርጋችሁ ዘንድ ጌታን ለምኑት፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**<u>ክፍል 3</u>**

***መግቢያ***:

የጳውሎስን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያስታውሱን ሌሎች አምስት ከተሞች አሉ እነርሱም፡ ተሰሎንቄ፣ቤሪያ፣አቴና፣ቆሮንቶስ እና ኤፌሶን ናቸው። እነዚህ ስሞች ለእናንተ እንግዶች ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት አምስቱ መጻህፍቶች የተጻፉት በእነዚህ ከተሞች ለሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት ነው። ማውጫውን በመመልከት የአምስቱንም ከተሞች ስሞች ቀጥሎ ጻፏቸው።

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

እስቲ በእነዚህ አምስት ከተሞች ውስጥ የተከናወኑትን ነገሮች በዝርዝር እንመልከት።

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት *ሥራ* 17:1-9 አንብቡ (በተሰሎንቄ)

***መልመጃ***:

1. ጳውሎስ የሰበከው ምን ነበር (ቁጥር 2-3)?

   ______________________________

   ______________________________

2. የስብከቱ ውጤት ምን ነበር (ቁጥር 4)?

   ______________________________

   ______________________________

3. ምን አይነት መከራና ስደት ደረሰ (ቁጥር 5-7)?

   ______________________________

   ______________________________

4. ክሱ ምን ነበር (ቁጥር 6፤ 7)

   ______________________________

   ______________________________

5. ለዚህ ክስ የሰዎቹ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 8-9)?

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 17:10-15 (በቤሪያ)

**መልመጃ**:

1. ስለ ቤሪያ ሰዎች ምን እንማራለን (ቁጥር 11)?
2. የጳውሎስ ስብከት ውጤት ምን ነበር (ቁጥር 12)?
3. ምን አይነት ስደትና መከራ ደረሰ (ቁጥር 13-15)?

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 17:16-34 አንብቡ (በአቴንስ)

**መልመጃ**:

1. በቁጥር 16 እና 21 ላይ ስለ አቴና እና አቴናውያን ምን እንማራለን?
2. ጳውሎስ ምን ሰበከ (ቁጥር 18)?

   ከቁጥር 24-31 ባለው ክፍል ጳውሎስ ስለማይታወቀው አምላክ ምን ነበር ያስተማረው?
3. የአንዳንዶች ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 32)?

   የሌሎችስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 32)?

እና (ቁጥር 34)?

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 18:1-17 አንብቡ (በቆሮንቶስ)

**መልመጃ**:

1. ጳውሎስ በአቴና የሚቀበለው ስላጣ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። በዚያ ማንን ነበር ያገኘው፣ለምን ነበር በቆሮንቶስ የሚኖሩት፣ ስለእነርሱ ምን ትማራላችሁ (ቁጥር 1-4)?

2. ጳውሎስ የሰበከው ምን ነበር (ቁጥር 5)?

3. ምን አይነት ስደትና መከራ ደረሰባቸው (ቁጥር 6)?

4. ጳውሎስ አገለግሎቱን በተመለከተ የገለጸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 6)?

5. ጳውሎስ ቀጥሎ ወዳለው ቤት ሲገባ ምን ነበር ያገኘው (ቁጥር 7-8)?

6. ጳውሎስ ሲያገለግል ከገጠመው ከባድ ችግር የተነሳ እጅግ ዝሎ ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር በምን መንገድ ባረከው (ቁጥር 9-11)?

7. ጋዮስ በአካያ ላይ አገረ ገዥ በነበረበት ወቅት ጳውሎስ ምን እንደገጠመው ተመልከቱ። አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው ተመካክረው ጳውሎስን ወደ ፍርድ ወንበር ፊት አመጡት። ክሳቸውም “ህግን ተቃውሞ እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ ሰዎችን ያባብላል” የሚል

ነበር፡፡ ነገር ግን ጋዮስ ጉዳዩን እራሳቸው እንዲፈቱ በመንገር ከፍርድ ቤት አስወጣቸው፡፡ አይሁድ ጳውሎስን ከማጥቃት ይልቅ ምን ነበር ያደረጉት ?

____________________________________________________

____________________________________________________

8. በ1ኛ ቆሮንቶስ 1:1 "በእግዚአብሔር ፈቃድ የ__________________ ሊሆን __________________ ጳውሎስ ወንድሙም __________________፥ ቁጥር 2 "፤በ__________________ ላለች __________________፥" እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በመመልከት ሶስቴን የሚባለው ሰው የጳውሎስ የጉዞ አጋሩ እንደሆነ መገመት እንችላለን፡፡

**<u>ክፍል 4</u>**

***ትምህርት***:

ጳውሎስ ሲጓዝ ሁልጊዜ በመጀመሪያ የሚሄደው ወደ አይሁድ ምኩራብ ሲሆን በዚያም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እና መከራን ይቀበል ዘንድ፣ ከሞትም ይነሳ ዘንድ እንደሚገባው ማረጋገጫ በመስጠት ከእነርሱ ጋር ይከራከራል፣ይሰብካል፡፡ ቃሉን ስለ መሲሁ የተናገረውን ያብራራላቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ሁልጊዜ ሁከት በመካከላቸው ይፈጠር ነበር፡፡ አንዳንድ አይሁዶች ያምኑ ነበር፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ አያምኑም ነበር፡፡ አንዳንድ ግሪኮች ያምኑ ነበር አንዳንዶች ደግሞ አያምኑም ነበር፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ከቅናት የተነሳ አመጽ እና ሁከት ያስነሱ ነበር፡፡ አንዳንዶች መልእክቱን ሰምተው ይቀበሏቸው ነበር፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በቁጣ ይሰድቧቸው ፣ልብሳቸውንም ይቀዱ ነበር፡፡ ይህንን ለጆሮአቸው እንግዳ የሆነ መልእክት አንዳንዶች ይቀበሉት ሌሎች ደግሞ ይገፉት ነበር፡፡ ሰዎች መልእክቱን እንደዚህም ይቀበሉት እንደዚያ ይህንን ሁሉ ምላሽ የሚያስተናግደው መልእክት የኢየሱስን ከሞት መነሳትና ህያው መሆን የሚናገረው መልእክት እንደሆነ አስታውሱ፡፡

ይኸው መልእክት በዚህም ዘመን እንደዚሁ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ መልእክቱን ዛሬም ቢሆን አንዳንዶች ይቀበሉታል፤ አንዳንዶች ደግሞ ይገፉታል፡፡ ምንም እንኳን አቴናውያን ከጳውሎስ ጋር መወያየት ቢፈልጉ ጳውሎስ ግን አቴናን ለቆ ወጥቷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የአቴና ሰዎች ሁልጊዜ ስራ ፈተው አዲስ የሆነ ሃሳብ መስማት እና ክርክር ማድረግ ልማዳቸው በመሆኑ ነበር፡፡ የሰዎችን ሃሳብ መስማትና መቃወም ልማድ ነበራቸው ፡፡ በመሆኑም ጳውሎስ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ጊዜ መፍጀት አልፈለገም፡፡

**ከህይወታችን ጋር ማዛመድ**: እንደዚህ ብለን ልንጠይቅ እንገደዳለን፡ ለዚህ መልእክት እኔ የሰጠሁት ምላሽ ምንድነው?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

**ትምህርት**:

1. ከቃሉ እንደተረዳነው ይህንን መልእክት ሰምተው አምነው የተቀበሉት እንደ ልድያ፣የእስር ቤቱ ጠባቂ ፣የምኩራብ ኃላፊ የነበረው ሰው ማመናቸውን ከቤተሰባቸው ጋር በመጠመቅ በተግባር ያሳዩ ነበር። ሌሎች ደግሞ ከዚህ አልፈው እንደ አቂላና ጵርስቅላ የጳውሎስ የጉዞ አጋር ሆነው ማገልገላቸውን ቀጥለዋል። ሌሎች ደግሞ አጵሎስን የመሳሰሉ ሰዎች ከሐዋሪያት ጋር አብረው በመጓዝ በእምነት አዲስ የሆኑትን በማስተማር ሌሎቹን ወንድሞችና እህቶች ደግሞ በማጽናናት በትጋት ያገለግሉ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ውስጥ ታድግና ትሰፋ ነበር።

    ሀ. የሐዋሪያት ሥራ 16:5 እንደዚህ ይላል፡

    "__________በሃይማኖት__________በ_______ ዕለት ዕለት ____________።

    ለ. የሐዋሪያት ሥራ 19:20 ደግሞ እንደዚህ ይላል "እንዲህም___________በኃይል ____________ እና ___________ነበር።

    ሐ. የሐዋሪያት ሥራ 19:17 እንደዚህ ይላል "በሁላቸውም ላይ __________________ ወደቀባቸው፥ የጌታም ___________________"

2. መፍረክረክ የሚታይባቸው አብያተ ክርስቲያናት በጳውሎስ፣በሲላስ፣በበርናባስ ፣በጢሞቴዎስ እና በሌሎችም መጽናናት ያስፈልጋቸው ነበር። ለምሳሌ በሐዋሪያት ሥራ 18:23 ጳውሎስ ከስፍራ ስፍራ እየተዘወዋረ ደቀ መዛሙርትን ያበረታታና አብያተ ክርስቲያናትን ያጠናክር እንደነበረ ተጽፎልናል። በወቅቱ ክርስቲያኖቹ ከባድ የሆነ የመከራ ጊዜ ያሳልፉ ስለነበር ጌታን ከመሰከሩላቸው ወንድሞች ዘንድ መጽናናት ያስፈልጋቸው ነበር።

3. በሐዋሪያት ሥራ 19:21 ጳውሎስ ወደ____________________ለመሄድ ወሰነ፡፡ በዚያው ጊዜ ደግሞ በኤፌሶን በክርስቲያኖች ላይ ስደት ተነስቶ ነበር፡፡ በመጨረሻው የጳውሎስ ጉዞ ላይ ያስተላለፈው መልእክት የብር አንጥረኛው ዲሜጥሪዮስ ላይ ችግር ፈጥሮበት ነበር፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ገቢ በብር ማዕድን ጣኦት እየሰራ ያቀርብላቸው የነበሩ የኤፌሶንና የእስያ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ብዙ ህዝቦች የጳውሎስን ትምህርት ሰምተው ተከትለውት ነበር (ቁጥር 26)፡፡ ጳውሎስ ምን ነበር እያለ የነበረው (የሐዋሪያት ሥራ 19:26)? "______________________________፡፡" የእነዚህ ሰዎች ሥራ የተናቀ ብቻ ሳይሆን የሚሆነው፥ እስያ ሁሉ ዓለሙም የሚያመልካት የታላቂቱ አምላክ _________________ መቅደስ ምናምን ሆኖ እንዲቆጠር እንጂ፥ _________________________ ደግሞ _________________________ ፈርተዋል፡፡

4. ከጳውሎስ በስተቀር ሁሉም በማጉረምረም ላይ ናቸው፡፡ ከጳውሎስ በስተቀር ሁሉም ሰው ተቆጥቷል፡፡ ህዝቡ ሁሉ በታላቅ ቁጣ እንደዚህ እያሉ ይጮኹ፡"_________________________________________________________________________" ከተሰበሰበው ህዝብ ግማሹ በሚሆነው ነገር ግራ ተጋብው ነበር፡፡ የሐዋሪያት ሥራ 19:32 እንደዚህ ይላል "በጉባኤው ድብልቅልቅ ሆኖ የሚበልጡት ስንኳ ስለ ምን እንደተሰበሰቡ አላወቁም ነበርና፡፡" "የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት" እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ጮኹ (ቁጥር 24)!" በመጨረሻም የከተማው ጸሐፊ "የኤፌሶን ከተማ ለታላቂቱ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣዖትዋ የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን የማያውቅ ሰው ማን ነው?" በማለት ህዝቡን ጸጥ አሰኘው፡፡ የመቅደስን ዕቃ ያልሰረቁ አምላካችንንም ያልሰደቡ እነዚህን ሰዎች አምጥታችኋቸዋልና" በማለት ተናገራቸው፡፡ የከተማው ጸሐፊ ፍርሃት ምን ነበር (ቁጥር 40)?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

__________ከዚያም ጉባኤው ተበተነ፡፡

## ትምህርት አራት

# ወደ አህዛብ ሂዱ

### የሐዋሪያት ሥራ 20-23 — መከራው

**የትምህርት ቅኝት 4**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4: የሐዋሪያት ሥራ 20-23

- በኤፌሶን የተደረገው እርዳታ
- የጳውሎስ ባህሪይ
- በኢየሩሳሌም የተነሳው አመጽ
- የጳውሎስ ህይወት መለወጥ ምስክርነት
- ጳውሎስ፡ የሮም ዜጋ
- የጳውሎስ መከራ

***መግቢያ***

ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ተሰናብቶ ፋሲካ ከመድረሱ በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቸኮለ፡፡ በዚያ ተቃውሞ ከመግጠሙ በፊት የነበረው የጳውሎስን ባህሪይ ጊዜ ወስዳችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡ ጳውሎስ ጌታ ከሰጠው *ሥራ* አንጻር መከራና ስደትን እንዴት እንደሚመለከተው እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን አካል ከሆኑት አማኞች የሚጠብቀውን እንደዚሁም ከእርሱ ጋር አብሮ ሰራተኛ ለሆኑት ያለውን ፍቅር ተመልከቱ፡፡

ከመጨረሻው ሚሲዮናዊው ጉዞው በኋላ ጳውሎስ "እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ያደረገውን እያንዳንዱን ነገር ለኢየሱስ ወንድም ያዕቆብና ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተረከላቸው፡፡" ይህንን የሰሙት ሰዎች ምላሽ ምን ይመስል እንደነበር ተመልከቱ፡፡

ወዲያውም በአይሁድ ልማድ መሰረት አንድን ግሪካዊ ወይንም አህዛብ ወደ ቤተመቅደስ ማምጣት ያንን ስፍራ እንደማርከስ ይቆጠር ስለነበር በዚህ ምክንያት የጳውሎስ ህይወት አደጋ ላይ ወደቀ፡፡ የጳውሎስ ድርጊት የፈጠረው ችግር ምን ነበር? ጳውሎስን የያዙት ሰዎች ምን ማድረግ ነበር የፈለጉት? ውጤቱ ምን ነበር? ይህንን ነገር በቅርበት ተመልከቱ፡፡ ይህንን ክፍል ስታነቡ ስለ ኢየሱስ መከራ መቀበልና መገደል ምን አስታወሳችሁ?

**ትምህርት 4**

**ክፍል 1**

***መልመጃ*:**

1. ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ከመሄዱ በፊት ምን አደረገ (የሐዋሪያት ሥራ 20:1)?

___

___

2. ለጳውሎስ ጉዞው ከጠበቀው በላይ ዘግይቶበት ነበር። በቁጥር ሶስት መሰረት ጉዞውን ያዘገየበት ምን ነበር?

___

___

3. በመጨረሻም ጢሮአዳ ከጉዞ አጋሮቹ ጋር እንደገና ተገናኘ (ቁጥር 4-6)። በሐዋሪያት ሥራ 20:7-12 የተከሰተው ክስተት ምን ነበር?

___

___

___

4. ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቸኩሎ ነበር (ቁጥር 13-16)። በቁጥር 16 መሰረት ለምን ነበር እንደዚህ የቸኮለው?

___

___

5. ቁጥር 17 ላይ ጳውሎስ ምን ነበር የላከው?

___

___

ሽማግሌዎቹ ወደ ኤፌሶን ከመሄድ ይልቅ ወደ ሚሊጢ መጡ። ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች ምን ነበር የነገራቸው?

ሀ. ቁጥር 18:

___

ለ. ቁጥር 19:

______________________________________________

ሐ. ቁጥር 20:

______________________________________________

መ. ቁጥር 21:

______________________________________________

6. ነገሮች ለጳውሎስ አስቸጋሪ ነበሩ፡፡______________________ጳውሎስን እንዲሄድ አስገደደው፡፡ ከከተማ ወደ ከተማ ሲዘዋወር የጌታ መንፈስ ምን እያለ ነበር ያስጠነቀቀው የነበረው (ቁጥር 23)?

______________________________________________

7. ጳውሎስ ህይወቱን እንደምን ነበር የሚቆጥረው (ቁጥር 24)?

______________________________________________

8. ከሁሉ በላይ ማድረግ የፈለገው ምን ነበር (ቁጥር 24)?

______________________________________________

______________________________________________

9. ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎችን ዳግም አላያቸውም ነበር፡፡ እንዲጠነክሩ ሩጫቸውንም በትእግስት እንዲሮጡ አበረታታቸው፡፡ ጳውሎስ ለሽማግሌዎቹ ምን ነበር ያላቸው?

ሀ. ቁጥር 28:

______________________________________________

ለ. ቁጥር 28:

______________________________________________

ሐ. ቁጥር 29-31:

______________________________________________

10. መለየት ቀላል አይደለም፡፡ ለእግዚአብሔርና ለጸጋው ቃል ካስረከባቸው በኋላ (ቁጥር 32) በቁጥር 36 እንደዚህ የሚል ነገር ተነግሮናል______________________________፡፡ ይህንም ብሎ ተንበርክኮ ከሁላቸው ጋር ጸለየ፡፡ ሁሉም እጅግ __________________፥ ጳውሎስንም __________________ __________________ ነበር፡፡

11. ሽማግሌዎቹን በጣም ያሳዘናቸው ምን ነበር (ቁጥር 38)?

______________________________________________

______________________________________________

12. እነርሱም ተሰብስበው መርከቡ ድረስ ከሸኙት በኋላ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ጢሮስ ደርሰውም መርከቡ ጭነቱን የሚያራግፈው በዚያ ስለሆነ በዚያ ብዙ ቀን ተቀመጡ። በዚያ የሚኖሩ ወገኖችም እስከ ባህሩ ዳርቻ ድረስ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ሸኟቸው (የሐዋሪያት ሥራ 21:5-6) ______________________________________________

______________________________________________________________________::

13. ከአንዱ ቦታ ወደሌላ ስፍራ እየተጓዙ ከአንዱ ቤት ወደሌላኛው እየገቡ በመጨረሻም ___________________________ ቤት ገቡ (ቁጥር 8)።

*ማስታወሻ* : በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ በሰማሪያ በድንቅና በተአምራት ያገለገለው እንደዚሁም፣ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወንጌል የሰበከው ይህ ፊሊጶስ ነው።

14. ምንም እንኳን በተለያዩ ነቢያቶች ጳውሎስ ችግር እንደሚገጥመው ቢነገረውም ጳውሎስ ግን አቋሙን ሳይለውጥ ወደ _____________________________ተጓዘ (ቁጥር 15)። በሐዋሪያት ሥራ 21:17 ላይ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን የተቀበለችበት መንገድ እንዴት ነበር?______________________________________________________________

15. ጳውሎስ ወደዚያ ሲደርስ በመጀመሪያ ምን ነበር ያደረገው (ቁጥር 18-19)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ቁጥር 18-19**: በጳውሎስ የህይወት ምልልስ ውስጥ የጳውሎስን ትክክለኛ ባህሪይ መመልከት እንችላለን። እስቲ ከሐዋሪያት ሥራ 20 ጥቂት ሃሳቦችን ትኩረት ሰጥታችሁ ተመልከቱ።

1. በቁጥር 23 ላይ እንደምናውቀው ጳውሎስ መከራ የሚደንቀው ሰው አይደለም። መንፈስ ቅዱስ እንደዚህ በማለት ተናግሮት ነበር

   ______________________________________________________________________::

2. በቁጥር 24 ላይ የጳውሎስን______________________ የማድረግ ምኞትና ጉጉት ሩጫውንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበለውን አገልግሎት። ያ አገለግሎት ምን ነበር?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

3. ጳውሎስ ካመኑት እንደዚሁም የመንፈሳዊው ነገር የበላይ ጠባቂዎች ከሆኑ ሰዎች ከእነርሱ የሚጠብቀው ነገር ነበር (ቁጥር 28 ለምሳሌ)።

____________________የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን _______________ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ____________________ አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። እነርሱንም ለራሳቸውና ለ_______________ እንዲጠነቀቁ አዘዛቸው።

4. በቁጥር 36-38 ጳውሎስ በወንጌል አብረው ሰራተኞች ለሆኑት ያለውን እውነተኛ ፍቅር እንመለከታለን። በኤፌሶን ያሉትን ሽማግሌዎች ሲለያቸው ምን አይነት ስሜት እንደተሰማውና በእንባ እንደተለያቸው እናስታውሳለን።

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. እስቲ የራሳችሁን ባህሪይ አስቡ። ምን አይነት ጠንካራ ባህሪይ አላችሁ?

____________________________________________________

____________________________________________________

2. አንድ ሰው ስለ መከራ ያላችሁን አመለካከት እንድትገልጹ ቢጠይቃችሁ ምን አይነት ምላሽ ይኖራችኋል?

____________________________________________________

____________________________________________________

3. መከራን መቀበላችሁ በህይወታችሁ ላይ ምን ልዩነት አምጥቷል?

____________________________________________________

____________________________________________________

## ክፍል 2

**መግቢያ**:

በእኛ ዘንድ ያለው ኃይላችን የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በጳውሎስ እስራት፣መከራ፣እና ወደ ሮም ጉዞ ላይ ያተኩራል። ህይወት ለጳውሎስ ቀላል እንዳልሆነ እናስታውሳለን። ጌታ ለሐናንያ ስለ ጳውሎስ ሲነግረው ስለስሙ ብዙ ዋጋ እንደሚከፍል ተናግሮት ነበር (የሐዋሪያት 9:15-16)። የጳውሎስ ጉዞ በሄደበት ሁሉ እግር በእግር እየተከተሉ ከሚያስቸግሩት እና እንቅፋት ከሚሆኑበት አይሁዳውያን የተነሳ አስቸጋሪ ነበር። ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ተሰዷል፣ተወግሯል፣ተደብድቧል፣ታስሯል፣ ወደ ወህኒም ተጥሏል። ሁልጊዜ ሞት በዙሪያው ቢሆንም እንኳን ጳውሎስ ወንጌልን መስበኩን አላቋረጠም ነበር።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 21:27-36 አንብቡ።

ይህንን ክፍል ስታነቡ የህዝቡ የቁጣ ልክ ምን ያህል የከፋ እንደነበረ መረዳት ትችላላችሁ። ምን ነበር እንደዚህ እንዲቆጡ ያደረጋቸው ?

**መልመጃ**:

1. እነዚህ አይሁዳውያን ከየት ነበር የመጡት(ቁጥር 27)? ጳውሎስን እንዴት ነበር ያወቁት?

   ______________________________________________

2. ህዝቡን______________________ጳውሎስን______________________ ።
3. ምን እያሉ ነበር የጮሁት? ክሳቸው ምን የሚል ነበር (ቁጥር 28)? የሚከተሉትን በመቃወም አስተምሯል:

   ሀ.______________________________________________

   ለ.______________________________________________

   ሐ.______________________________________________

4. ሌላኛው ክሳቸው ምን ነበር (ቁጥር 28)?

   ______________________________________________

5. ከቁጥር 30-32 ያለውን ክፍል ትእይንት ግለጹ:

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

አመጹ የተካሄደው የት ነው?__________________የከተማውስ ስም? ________________?

6. ጳውሎስ ሳይገደል የቀረው በምን ምክንያት ነው?

   ______________________________________________

7. የወታደሮቹ አዛዥ ምን አደረገ (ቁጥር 33)?

   ______________________________________________

8. ከዚያም ስለተፈጠረው ትክክለኛ ነገር ለማወቅ ነበር የፈለገው። ከዚያስ ከምርመራው ምን አደረገ (ቁጥር 34)?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

9. እስቲ በህዝቡ መካከል ያነበረውን ግርግር ግለጹት(ቁጥር 35):

______________________________________________________________

______________________________________________________________

10. ህዝቡ ምን እያለ ነበር የሚጮኸው (ቁጥር 36)?

______________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

1. በኢየሩሳሌም የነበረውን ሁኔታ በጣም የሚያስገርም ነበር። ለመሆኑ የዚህ ብጥብጥ መነሻ ምን ነበር ? ጳውሎስ እግዚአብሔርን በመታዘዝ በመላው ትንሹ እስያ (የአሁኑ ቱርክ) እና በአካባቢው ባሉት ሃገሮች በሙሉ በሚቃወሙት መካከል ስለኢየሱስ ይመሰክር ነበር። ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ማንን ነበር የሚቃወሙት? እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን አመለካከት ግለፁ፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. በቁጥር 36 ላይ ያለውን ቃል ሰምተናል። ሉቃስ 23:18 እና ዩሐንስ 19:15። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የተከሰተውን ነገር ግለጹ።

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄ**: ሰዎች ሲቃወሟችሁ ወይንም ሲያጠቋችሁ ለእነርሱ መስጠት ያለባችሁ ምላሽ ምን ሊሆን ይገባል ብላችሁ ታምናላችሁ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## <u>ክፍል 3</u>

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት ሥራ 21:37-22:21 አንብቡ። በመጀመሪያ ጳውሎስ ስለራሱ ማንነት ይናገራል። ከዚያም ምስክርነቱን ይሰጣል።

**መልመጃ**:

1. ጳውሎስ ምስክርነቱን ለመስጠት ፈልጓል፡፡ በቁጥር 37 ላይ ምን ጠየቀ?

_______________________________________________

2. በቁጥር 40 ላይ ጳውሎስ ለህዝቡ እንዲናገር ፈቃድ ጠየቀ፡፡ በዚያ ስፍራ ንግግር ለማድረግ የተጠቀመው ቋንቋ ምን ነበር ? ____________________ ይህ ቋንቋ በዚያ ስፍራ የተሰበሰበው ህዝብ የሚሰማው ቋንቋ ነበር፡፡ በክፍሉ ላይ እንደምናነበው ጳውሎስ መናገር ሲጀምር ህዝቡ ያደመጠው በ____________________ ነበር፡፡

3. ጳውሎስ ያካፈላቸውን ነገር ከግንዛቤ ውስጥ አስገቡ:

ሀ. በመጀመሪያ ስላለፈው ታሪኩ ስለ አባቶቹ ተናገረ (ቁጥር 3):

_______________________________________________

_______________________________________________

ለ. የጳውሎስ የትምህርት ደረጃ ምን ነበር (ቁጥር 3)?

_______________________________________________

ሐ.የቀድሞው ባህሪው ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 4-5)?

_______________________________________________

_______________________________________________

መ. ቀጥሎ ደግሞ በ____________________መንገድ ላይ እንዴት ጌታን እንደተገለጠለት ነገራቸው፡፡

የኢየሱስ ጥያቄ:

_______________________________________________

የሳውል መልስ:

_______________________________________________

የኢየሱስ ጥያቄ:

_______________________________________________

የሳውል መልስ:

_______________________________________________

የኢየሱስ ጥያቄ:

_______________________________________________

ሠ. ከቁጥር 12-16 ባለው ክፍል ውስጥ ከአናንያ ጋር የነበረውን ነገር ግለፁ:

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ረ. ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ምን እንደገጠመው ተናገረ (ቁጥር 17-20)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ሰ. ጌታ ምን እንዲያደርግ አዘዘው (ቁጥር 21)?

______________________________________________

**ማሰላሰል**:

1. ጳውሎስ ስለመለወጡ በዝርዝር መናገሩን ቀጠለ። ምናልባት ጳውሎስ በተለወጠበት ተአምራዊ መንገድ የተለወጡ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። ጌታ ኢየሱስ እራሱ ነበር የጠራው! የመለወጡ ምክንያት ደግሞ ደማቁ ብርሃን፣የአይኑ መታወር፣የሰማው ድምጽ ፣ወይንም ሌላ ነበር አይደለም። ለውጡ የተከናወነው የጳውሎስ ልብ ውስጥ ነው። እስጢፋኖስ ተወግሮ ሲገደል ከመተባበር ጀምሮ ደብዳቤ በማጻፍ ይህንን መንገድ የሚከተሉትን ሰዎች በመደብደብ፣በማሰር እና በማሳደድ ይታወቅ የነበረ ሰው አሁን ለዚያው መንገድ ይደበደባል፣ ይታሰራል፣ይሰደዳል አሁን በሙሉ ልቡ የዚህ መንገድ ተከታይ ነው፣ ተጠምቋል። ኃጢአቱ በክርስቶስ ደም ተወግዶለታል። የጌታን ስም ይጠራል።

   ሀ. ምስክርነቱን በአረማይክ ቋንቋ መናገሩ ንግግሩን ምን ያህል በአድማጮቹ ዘንድ ዋጋ እንዲኖረው አድርጎታል?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ለ. እናንተና እኔስ ልባችን የተለወጠበትን ሁኔታ መመስከር እንችላለን?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ሐ. የእኔ ምስክርነት ለሚሰሙኝ ሰዎች ምን ያህል ዋጋ ይኖረዋል?

   ______________________________________________

_______________________________________________

2. በሐዋሪያት ሥራ 22:21 ጌታ ለጳውሎስ ምን ብሎ ተናገረው ይለናል "ሂድ፥ እኔ ወደ _____________ ከዚህ _____________እልክሃለሁና አለኝ።" ጳውሎስ ቀሪውን ዘመኑን በሙሉ የኖረው እንደተላከ ሰው ነው። የተልእኮ ሰው ነበር። እግዚአብሔር አህዛብን እንደዚሁም የጠፉትን ሁሉ እንዲደርስ ነበር የላከው! እግዚአብሔር አህዛብን ለመድረስ እውነተኛ እና ተልእኮውን በታላቅ ትጋት የሚወጣለት የተለወጠ ልብ ይፈልጋል። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ:

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. ምን ያህል ጉጉት አላችሁ? ለእግዚአብሔር ነገር ምን ያህል ትቀናላችሁ? እግዚአብሔር ለሚሰጣችሁ ተልእኮ ምን ያህል ቅናትና መቃጠል ውስጣችሁ አለ? እግዚአብሔር እንደላከው ሰው ስትኖሩ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ተልእኮ ስትወጡ ታላቅ የሆነ ደስታ ይሰማችኋል? ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም ስደትና መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች ናችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. የጠፉትን ለመድረስ እግዚአብሔር እናንተን ሊመራ በሚፈልግበት መንገድ ሁሉ ለመመራት ምን ያህል ፈቃደኞች ናችሁ፤ እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለጹ?

_______________________________________________

_______________________________________________

**ክፍል 4**

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 22:22-29 አንብቡ። ይህ ታሪክ ለሮማውያን ባለስልጣናቶች ችግር የሚፈጥር ነገር ተከስቶ እንደነበረ ይነግረናል።

**መልመጃ**:

1. ጳውሎስ በቁጥር 21 ላይ እግዚአብሔር እሩቅ ወዳሉ አህዛብ እንሚልከው እንደተናገረው ይነግረናል። ጳውሎስ ይህንን እስኪናገር ድረስ በጸጥታ እየሰሙት ነበር። ከቁጥር 22-24 ባለው ክፍል ውስጥ ምን ተከናወነ?

    ______________________________________________

    ______________________________________________

2. ጳውሎስን ጎተቱት ሊገነጣጥሉትም ፈለጉ። የጳውሎስ ጥያቄ ምን ነበር (ቁጥር 25)?

    ______________________________________________

3. የመቶ አለቃው ለሻለቃው የሆነውን ነገር አስረዳው፣ "ይህ ሰው ________________________ ነውና ________________________ተጠበቅ ብሎ ነገረው።"

    የሮማዊ ዜጋ የሆነ ሰው በድብደባ፣ በግርፋትና በስቅላት አይቀጣም። ይህ እንዳይሆንባቸው በሮማውያን ህግ ይጠበቃሉ። አሁን ግን ችግር ገጥሟቸዋል። ሻለቃው የጳውሎስን ሮማዊነት ለማረጋገጥ ጥያቄ ጠየቀው። በእርግጥም ጳውሎስ ሮማዊ ነው። እንደዚህ በማለት ነበር የተናገረው "የሮም ዜጋ የሆንኩት በ ______________________ነው።"

4. ጳውሎስን እንዲመረምሩ የተላኩት ሰዎች ወዲያውኑ ከእርሱ ____________________(ቁጥር 29)። ሻለቃው እራሱ __________________ነበር። ለምን ? ______________________።

**<u>ክፍል 5</u>**

**መግቢያ**:

የጳውሎስ መከራ ጀመረ። የጳውሎስን መከራ ስትመለከቱ ከኢየሱስ መከራ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ታገኙታላችሁ። ከእግዚአብሔር እውነት አንጻር ሲታይ ምንም አይነት በደል የለበትም፤ ከአይሁዶች አንጻር ሲታይ ግን ህጋቸውን ተላልፏል። በሐዋሪያት ሥራ 21:36 ላይ ህዝቡ ሁሉ "አስወግደው!" "በህይወት አይኑር!" እያሉ ይጮኹ ነበር። ይህ ጩኸታቸው "ስቀለው፣ስቀለው!" ከሚለው ጩኸት ጋር ተመሳሳይ ነበር። ቀጣዮቹ የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፎች ስለዚህ መከራ ይዘግባሉ። አይሁዳውያን የሚፈልጉት እንዲሞት ሲሆን ሮማውያን

ደግሞ የእነርሱን ህግ በተመለከተ ምንም አይነት ችግር ስላላገኙበት ምን ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 22:30-23:11 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ሻምበሉ ፊት ለፊት ለመነጋገር ጊዜው አሁን እንደሆነ አስቧል። ምን ነበር ማወቅ የፈለገው (ቁጥር 30)?

   ______________________________________________

2. በቁጥር 23፡1 ላይ ጳውሎስ ምን ነበር መግለጽ የፈለገው?

   ______________________________________________

3. ምን ነበር ሐናንያ የታዘዘው (ቁጥር 2)?

   ______________________________________________

4. ሐናንያ ሊቀ ካህን መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ጳውሎስ ምን አደረገ (ቁጥር 3)?

   ______________________________________________

5. ፈሪሳውያን እንደዚሁም ሰዱቃውያን በዙሪያው እንዳሉ ጳውሎስ አወቀ። በቁጥር 6 መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል መለያየትን ያመጣው ቀጥሎ ያደረገው ነገር ምን ነበር?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

6. ከቁጥር 9-10 ባለው ክፍል ውስጥ የተገለጸውን ቀጥሎ የተፈጠረውን ትእይነት ግለጹ:

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

7. አይሁዳውያኑን ይበልጥ ያበሳጫቸው ጌታ አናገረኝ በማለቱ ነው ወይንስ እነርሱ ለእግዚአብሔር የተመረጡ ህዝቦች እንዳልሆኑ ወደ ሚቆጥሯቸው ሰዎች በመላኩ ነው? የትኛው እንደሆነ ታስባላችሁ ፣ለምንስ እንደዚህ አሰባችሁ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

8. ሻለቃው እንደገና ለጳውሎስ ህይወት ሰግቶ ከሸንጎው እንዲወጣ አደረገው። በዚያ ምሽት ምን ተከናወነ (ቁጥር 11)?

______________________________________________________

______________________________________________________

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት ሥራ 23:12-22 አንብቡ።

***መልመጃ***:

1. እቅዱ ምን ነበር ይህንን ያደረጉት እነማን ነበሩ(ቁጥር 12-15)?

______________________________________________________

2. ይህንን እቅዳቸውን ማን ሰማ (ቁጥር 16)?

________________________________

3. በሰማው መረጃ ምን አደረገ (ቁጥር 17-21)?

______________________________________________________

______________________________________________________

4. ለጳውሎስ የእህት ልጅ ሻለቃው ምን እንዲያደርግ ነገረው (ቁጥር 22)?

______________________________________________________

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት ሥራ 23:23-35 አንብቡ

***መልመጃ***:

1. ሻለቃው ቀጥሎ ምን እንዲደረግ ትእዛዝ ሰጠ (ቁጥር 23-24)?

______________________________________________________

______________________________________________________

2. ቂሳርያ የሰማሪያና የይሁዳ ገዢዎች የሚቀመጡባት የሮም ማዘዣ ጣቢያ ናት። በወቅቱ የነበረው የሮም ገዢ ፊልክስ ይባል ነበር። ሻለቃው ጳውሎስ በፊልክስ ፊት በደህና ለፍርድ እንዲቀርብ እንዲጠብቁት ወታደሮቹን ፣ፈረሰኞችን ፣እንደዚሁም የጦር መሳሪያ የታጠቁትን ሁሉ አዘጋጀ።
3. ቀላውዲዮስ ሉስዮስ ለገዢው የጻፈውን መልእክት በአጭሩ ግለጹት (ቁጥር 27-30)።

______________________________________________________

4. ወታደሮቹ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ተቀብለው ጳውሎስን በአጀብ ወደ ፊልክስ ወሰዱት። ፊልክስ ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ ምን ለማድረግ ወሰነ (ቁጥር 35)?

# ትምህርት አምስት

# ይሰማሉ

## የሐዋሪያት ሥራ 24-28 — ሮም

---

### የትምህርት 5 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 5: የሐዋሪያት ሥራ 24-28

- ጳውሎስ በፊልክስ ፊት
- ጳውሎስና ፊጦስ
- የጳውሎስ መከላከያ
- ጉዞ በመርከብ ወደ ኢጣሊያ
- የባህሩ ማእበል
- በመጨረሻ ሮም
- የታወቀ ይሁን

### መግቢያ

ጳውሎስ ወደ ሮም ያደረገው ጉዞ ረጅምና አስቸጋሪ ነበር። በንጉስ ፊልክስ ፊት፣ከዚያም ፊጦስ ፊት አሁን ደግሞ በንጉስ አግሪጳ ፊት መከራዎችን ተጋፍጧል። ይህንን ክፍል ስታጠኑ በመርከብ ተጉዞ ሮም መግባቱን ትረዳላችሁ። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በማቅናት የመስቀሉን መከራ በጽናት ተጋፍጦታል። ጳውሎስ ደግሞ በጽናት ወደ ሮም በመጓዝ ላይ ነው።

የጳውሎስን ብልጠት የተሞላበት አነጋገር ተመልከቱ። እድሉን ተጠቅሞ እግዚአብሔር በህይወቱ የሰራውን ነገር ነገራቸው። ወደ ዳኛው ሲቀርብ ጌታ "ስለ ስሜ ትመሰክራለህ" ያለው ቃል ፍጻሜ እንደሚያገኝ አምኖ ነበር። ይህንን እድል በመጠቀም እግዚአብሔር የሰራለትንም የራሱንም ንጽህና የመሰከረው።

ገዢውም ሆነ ንጉሱ ስለ ጳውሎስ የተናገሩትን ነገር ተመልከቱ። ወደ ሮም በመርከብ የተጓዘበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ተመልከቱ። ዘግይታችሁም ቢሆን ሮም በመድረሳችሁ ደስ ይበላችሁ አሁን ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ እንደተማረው "በግልጽነትና ያለ ፍርሃት" በሁሉ ፊት ሲመሰክር ለመስማት ተዘጋጁ።

**ትምህርት 5**

**<u>ክፍል 1</u>**

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 24 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. በሊቀ ካህናቱ ሐናንያና በጠበቃው ጠርጠሉስ አማካይነት በጳውሎስ ላይ በፊልክስ ፊት ያቀረበው ክስ ምን ነበር (ቁጥር 5-8)?

   ሀ. ቁጥር 5

   ________________________________________________

   ለ. ቁጥር 5

   ________________________________________________

   ሐ. ቁጥር 6

   ________________________________________________

   በዙሪያው የተሰበሰቡት አይሁዳውያንም ክሱ እውነት መሆኑን በሐሰት ይመሰክሩ ነበር (ቁጥር 9)፡፡

2. በማጠቃለያውም ጳውሎስ ምን በማለት እራሱን ተከላከለ (ቁጥር 10-21):

   ሀ. ቁጥር 14

   ________________________________________________

   ለ. ቁጥር 15

   ________________________________________________

   ሐ. ቁጥር 16

   ________________________________________________

3. በተጨማሪም ጳውሎስ የከሳሾቹን ክርክር አፈረሰባቸው (ቁጥር 18): “ይህንም ሳደርግ ሳለሁ ሕዝብ ሳይሰበሰብ ሁከትም ሳይሆን በመቅደስ ስነጻ አገኙኝ፡፡”

4. በቁጥር 21 ጳውሎስ በዚህ ችግር ውስጥ እንዲያልፍ አንደኛው ምክንያት ምን እንደሆነ ነው የተናገረው ?

   ________________________________________________________

   ________________________________________________________

5. ፊልክስ ስብሰባው ለጊዜው እንዲቆም አደረገ። ውሳኔው ምን ነበር (ቁጥር 22-23)?

____________________________________________

በቁጥር 22 ላይ እንደምናነበው ፊልክስ "የመንገዱን ነገር አጥብቆ ማወቁ" በጣም ደስ የሚል ነገር ነው።

6. በፊልክስና በጳውሎስ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ተፈጥሯል። ፊልክስ ወደ ጳውሎስ መልእክት ላከተበት። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ስለምንድነው የሚናገረው (ቁጥር 24-25)?

____________________________________________

በሌላ መልኩ ደግሞ ፊልክስ ከጳውሎስ የጠበቀው ነገር ነበር። ምን ነበር ፊልክስ ከጳውሎስ ጠብቆ የነበረው (ቁጥር 26)?

____________________________________________

7. ሁለት አመታት አለፉ። በፊልክስ ፈንታ ገዢ ሆነ የተሾመው ማነው (ቁጥር 27)? ____________ ፊልክስ ሳይጨርስ ወደ ፊስጦስ ያስተላለፈው ነገር ምን ነበር?

____________________________________________

**የቤት ሥራ** : የሐዋሪያት ሥራ 25 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ቂሳርያ እንደደረሱ ወዲያውኑ____________________________
   በዚያ ምን ሆነ (ቁጥር 2)? ____________________________
2. የአይሁድ መሪዎች ምን አደረጉ (ቁጥር 3)? ____________________
3. ምን ነበር ያቀዱት (ቁጥር 3)?

   ____________________________________

4. ፊስጦስ ምን ነገራቸው (ቁጥር 4-5)?

   ____________________________________________

5. አሁን ችሎቱ ተዘጋጅቷል። ከቁጥር 7 ምን እንማራለን?

   ____________________________________________

6. ጳውሎስ መከላከያውን ያቀረበው ምን በማለት ነበር (ቁጥር 8)?

   ____________________________________________

7. በቁጥር 9 ላይ ስለ ፊስጦስ ምን እንረዳለን? ጳውሎስን ምን ጠየቀው?

______________________________________________________________

8. ከቁጥር 10-11 ባለው ክፍል ውስጥ ምን ተነጋገሩ?

______________________________________________________________

9. ጳውሎስ ለቄሳር ይግባኝ አቀረበ። ፌስጦስም ከጉባኤው ጋር መክሮ እንደዚህ በማለት ተናገረ፡“______________________________________________________________

______________________________________”

**ገለጻ**:

በቁጥር 11 ላይ “አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ” የሚል ቃል እናገኛለን። ይህ ቃል አሁንም የኢየሱስን መከራ ያስታውሰናል። ለሐናንያ ከዚያም ለቀያፉ ከዚያ ለጲላጦስ ከዚያም ለሄሮድስ ተላልፎ ተሰጠ ተመልሶ ለጲላጦስ ተላልፎ ተሰጠ። በመጨረሻም ለሚሰቅሉት ሰዎች ተላልፎ ተሰጠ (ዮሐንስ 19:16)። ማንም ከኢየሱስ ጋር ምን ማድረግ እንደሚገባው ለአላወቀም ነበር ። ልክ እንደዚሁ ከጳውሎስ ጋርም ምን ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም። እኛም እንደዚሁ ብዙ እድሎች ተሰጥተውናል ስለዚህ ምን ማድረግ እንደሚገባን ማወቅ አለብን። ከኢየሱስ ጋር ምን ማድረግ ነው ያለብኝ። ተቀብዮው የዘላለም ህይወት ፤እና ድነት ማግኘት ወይንስ ለሌሎች አሳልፎ መስጠት ከዚያም ከእርሱ ጋር ሊኖረኝ የሚገባውን ግንኙነት እንደዚሁ ለሌሎች አሳልፎ መስጠት? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን አስተያየት:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

<u>**ክፍል 2**</u>

**ትምህርት**:

ፌልክስ የጳውሎስን ጉዳይ ሳይደመድም ማለፉ ፌስጦስን ትንሽ ሳያበሳጨው እንዳልቀረ መገመት እንችላለን። እርሱስ የጳውሎስን ጉዳይ ምን ሊያደርግ ይሆን? አይሁዳውያን ጳውሎስ ላይ እንዲፈረድበት ነበር የፈለጉት፤ ፌስጦስ ግን በሮማውያን ህግ መሰረት አንድ ሰው ክስ ሲቀርብበት በቅድሚያ ክሱን በአደባባይ እንዲከላከል እድል እንዲሰጠው ይደነግጋል። ስለዚህ

የጳውሎስም ጉዳይ በዚሁ መንገድ እንዲታይለት ነበር የፈለገው። ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድ ይልቅ ጳውሎስ ጉዳዩ በሮም እንዲታይለት ይግባኝ ብሎ ነበር። ፊስጦስ ያለውን ሃሳብ ቂሳርያን ሊጎበኝ ከበርኒቄ ጋር ለመጣው ለአግሪጳ ነገረው። ፊስጦስ የጳውሎስና የአይሁዳውያን ችግር ስለህጋቸው መከራከር እንደሆነ ለአግሪጳ ነገረው። እንደሚታወቀው ፊስጦስ ጳውሎስ ስለሚያወራለት "የሞተው አሁን ደግሞ ከሞት ተነስቷል እያለ ስለሚናገርለት ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው" ምንም አያውቅም። ለመሆኑ እርሱ ማነው? በሐዋሪያት ሥራ 25:22 አግሪጳ ለፊስጦስ እንደዚህ በማለት ተናገረው "____________________________________።"

**መልመጃ**:

1. ጳውሎስ ሲገባ የጉባኤው ድባብ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 23)? ________________

   ____________________________________________________________________

2. ፊስጦስ ተናገረ። የዚህ ስብሰባ ዋና አጀንዳ ምን ነበር (ቁጥር 24-27)?

   ____________________________________________________________________

3. ጳውሎስ ሃሳቡን የሚያቀርብበት እድል ተጥቶታል። እስቲ የመክፈቻ ንግግሩን ሃሳብ ጠቅለል አድርጋችሁ አቅርቡ (የሐዋሪያት ሥራ 26:4-8)?

   ____________________________________________________________________

4. ለምንድነው ጳውሎስ በመከራ ላይ እንደሆነ ያሰበው (ቁጥር 8)?

   ____________________________________________________________________

5. የጳውሎስ ያለፈ ህይወት ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 9-11)?

   ____________________________________________________________________

6. ከቁጥር 12-18 ባለው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ህይወቱ የተለወጠበትን ምስክርነቱን ተናገረ። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በህዝቡ ፊት በቀረበበት ወቅት የተናገረውን ንግግር ነበር በዚህም ስፍራ በድጋሚ የተናገረው (የሐዋሪያት ሥራ 22)። ከቁጥር 15 እስከ 18 ያለውን ክፊል ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። ኢየሱስ ለጳውሎስ የተናገረውን ነገር ልብ በሉ።

   ሀ. ቁጥር 16: ________________ፊት ለፊት ________________ ለተከሰሰበትም መልስ ይሰጥ ዘንድ _________________________ ሳያገኝ፥ ማንንም ቢሆን አሳልፎ መስጠት ________________አይደለም ብዬ መለስሁላቸው።

ለ. ቁጥር 17: ስለዚህም በዚህ ____________________ ጊዜ፥ ሳልዘገይ በማግሥቱ ____________________ተቀምጬ ያንን ሰው ያመጡት ዘንድ አዘዝሁ።

ሐ. ቁጥር 17-18: ስለዚህም በዚህ _______________ ጊዜ፥ _______________ በማግሥቱ _______________ተቀምጬ ያንን ሰው _______________አዘዝሁ።_______________ በቆሙ ጊዜ እኔ _______________ ክፉ ነገር _______________ ምንም አላመጡበትም፤

7. ጳውሎስ በዚያ ስፍራ የተናገረው ነገር የሚሰብከውን ስብከት ነው (ቁጥር 20)?

ሀ. የሰማዕትህንም ____________________________________ጊዜ፥

ለ. ራሴ ደግሞ ________________________________________

ሐ. __________________ የገዳዮችን __________________አልሁ።

8. ጳውሎስ ስለ ምስክርነቱ ምን ነበር ያለው (ቁጥር 22-23)?

________________________________________________________________________

9. ፊስጦስ የጳውሎስን ንግግር ጮኾ እንደዚህ በማለት አስቆመው: "_________________ ________________________________________________________________________"

10. ጳውሎስ ለፊስጦስ የሚናገረው ነገር የውሸት ሳይሆን እውነተኛና ምክንያታዊ እንደሆነ ነገረው። ምን ነበር ወደ አግሪጳ የመራው (ቁጥር 26)?

________________________________________________________________________

11. አግሪጳን ምን አይነት ጥያቄ ነው የጠየቀው (ቁጥር 27)?

________________________________________________________________________

12. የአግሪጳ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 28)? ________________________________________

________________________________________________________________________

13. የጳውሎስ ምላሽ ምን ነበር?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

14. ከዚያም ፊስጦስ፣ንጉስ አግሪጳ፣በርኒቄስ እና ከእነርሱ ጋር የተቀመጡት በሙሉ ክፍሉን ለቀው ወጡ። ምን ነበር የተወያዩት (ቁጥር 31)?

________________________________________________________________________

15. አግሪጳ ለፊስጦስ ምን ሲለው ነው የሰማነው?

________________________________________________________________________

**ክፍል 3**

***ገለጻ***:

እስቲ ለአፍታ ንጉሱ ፣የከተማይቱ ገዢ ፣እንደዚሁም ከፍተኛ ባለስልጣናት በተገኙበት ህዝብ በተሰበሰቡበት ጉባኤ መካከል ተከሳሹ ጳውሎስ እየተራመደ ሲገባ በምናባችሁ አስቡት (የሐዋሪያት ሥራ 25:23)። እስቲ እናንተ ጳውሎስን ብትሆኑ ኖሮ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ይሰማችሁ ነበር? ስለዚህ ሰአት ወደ አእምሯችሁ ምን አይነት ሃሳብ ይመጣ ነበር? ፍርሃትና ድንጋጤ ይታይባችሁ ይሆን? ስሜታዊ? የተጨነቀ? ጳውሎስ ምን አይነት ስሜት ምን አይነት ስሜት የተሰማው ይመስላችኂል? የሐዋሪያት ሥራ 26:2 አንብቡት። ጳውሎስ ህዝቡን በምን መንገድ ነው የሚመለከተው? ጳውሎስ መከላከያውን ሲያቀርብ በንግግሩ ውስጥ ድክመት ወይንም ጥንካሬ አግኝታችሁበታል? ጳውሎስ ተስፋውን ለህዝቡ ሁሉ የሚናገርበት እንዴት ያለ ትልቅ እድል ነው ያገኘው! ጳውሎስ እንደነጻ ሰው ተዘጋጅቶ ነበር የቀረበው፤ ህሊናውም ንጹህ ነበር። ለእግዚአብሔር እንዲሰራለት የጠራውን ስራ ታሪክ ለመመስከር ነጻ ነበር። ይህ ሰው ከጨለማ ወደ ብርሃን ይመጡ ዘንድ የሰዎችን አይን ይከፍት ዘንድ ከሰይጣን ግዛት ወደ እግዚአብሔር ግዛት ይመልስ ዘንድ የኃጢአትን ስርየት ይቀበሉ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ከተቀደሱት ጋር መኖር እንዲችሉ ያደርግ ዘንድ ተልእኮን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለ ሰው ነው።

***ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄ***: የተሰጠኝን ታላቅ ተስፋ ለሰዎች የምገልጽበት እድል ያገኘሁባቸው ሁኔታዎች ምንድነው ?

________________________________________

________________________________________

***ጸሎት***:

ኦ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ጳውሎስን እንደላከው ሁሉ እኔንም አንተን ወደማያውቁ ሰዎች ልከኸኛል። ወደ እነርሱ በአላማ ልከኸኛል። አይናቸውን እንድከፍትና ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድመልሳቸው ልከኸኛል። ከሰይጣን መንግስት ወደ እግዚአብሄር እመልሳቸው ዘንድ በእምነት ከዳኑት ቅዱሳን ጋር መኖር እንዲችሉ መንገድን አሳያቸው ዘንድ ልከኸኛል። ለሰጠኸኝ ታላቅ ስራ አጠንክረኝ። በሰጠኸው ተስፋ እንደሚኖር ሰው የምስራቹን በድፍረትና በግልጽ መናገር እችል ዘንድ እርዳኝ።

---

## ክፍል 4

***መግቢያ***:

በመጨረሻም ወደ ኢጣሊያ በመርከብ ለመሄድ ተወሰነ (የቤት *ሥራ* 27:1 አንብቡት)። ጳውሎስ እና ሌሎቹ እስረኞች የአውግስጦስ ጭፍራ ለሆነው ዩልዩስ ለሚባለው መቶ አለቃ በኃላፊነት ተሰጡት። ከጳውሎስ *ጋር* እነማን እንደሄዱ ባናውቅም ነገር ግን አርስጥሮኮስ አብሮት ነበረ። እንደዚሁም “እኛ” እያለ በመጻፉ ምክንያት ሉቃስ አብሮት እንዳለ እንገምታለን። አርስጥሮኮስን ታስታውሱ እንደሆነ ጳውሎስ ከመቄዶንያ አብሮት የተጓዘ ኤፌሶን አመጽ ሲነሳ ከጳውሎስ *ጋር* አብረው የነበረ ነው (የሐዋሪያት *ሥራ* 19:29)።

**የቤት *ሥራ***: የሐዋሪያት *ሥራ* 27:1-12 አንብቡ

***መልመጃ***:

1. በቁጥር 3 ላይ የጳውሎስና የዩልዩስ ግንኙነት ምን ነበር ?

   ጳውሎስ መርከቡ እስኪነሳ ድረስ ወንድሞችን ጎብኝቶ እንዲመለስ ነጻነት የተሰጠው ይመስላል እንጂ በሰንሰለት ታስሮ በወታደሮች በጥብቅ እንዲጠበቅ የተደረገ አይመስልም።

2. ከቁጥር 4- 12 ባለው ክፍል ውስጥ ስታነቡ ወዲያውኑ የምትረዱት ነገር ምንድነው? በባህሩ ላይ የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ?

   ሀ. ቁጥር 4:

   ለ. ቁጥር 7:

   ሐ. ቁጥር 7:

______________________________________________

መ. ቁጥር 7:

______________________________________________

ሠ. ቁጥር 8:

______________________________________________

ረ. ቁጥር 9:

______________________________________________

3. የባህር ጉዞው ሲጀመር ብዙ ጊዜ እንደፈጀና በባህር ለመጓዝ ጥሩው ወቅት አልፎ እንደነበር እናውቃለን። እነ ጳውሎስ የተጓዙበት ወቅት ለባህር ጉዞ አመቺው ወቅት አልነበረም (ቁጥር 9)። በቁጥር 10 ላይ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

4. መቶ አለቃው፣የመርከቡ ባለቤት እንደዚሁም ፣መርከበኛው የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ሊቀበሉ አልወደዱም ነበር። የብዙዎቹ ውሳኔ ምን ነበር (ቁጥር 12)?

______________________________________________

______________________________________________

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 27:13-26 አንብቡ።

**መልመጃ**:

1. ንፋሱ በሃይል መንፈስ በጀመረ ጊዜ ማዕበሉ መርከቡን ማናወጥ ጀመረ። አሁን በማዕበል በምትንገላታው መርከብ ውስጥ ተግዳሮቱ ቀጥሏል። ነፋሱም በርትቶ ሲያስጨንቀን በማንግሥቱ ከጭነቱ________________________(ቁጥር18)።

   ቁጥር 19__________________________________መወርወር ጀመሩ።

2. የንፋሱ ማየል የማዕበሉም መበርታት ብቻ ሳይሆን መርከቡን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ለመምራት የሚረዳ ፀሐይም ሆነ በምሽት ኮከብ አልነበረም። ስለዚህ መርከቡ አቅጣጫውን ስቶ ነበር። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ የሚገጥማቸው ጭንቀት ብቻ አይደለም (ቁጥር 20)?

3. ከዚያም የጳውሎስ “ነግሬያችሁ ነበር” የሚለው ንግግር ተከተለ፡፡ ምን ነበር የነገራቸው (ቁጥር 21)?

4. ጳውሎስ ሰዎቹን ያጽናናቸው ነበር(ቁጥር 22):

5. የመልአኩ መልእክት ምን ነበር (ቁጥር 23-24)?

6. በቁጥር 25 ላይ የምስራቹ ምን ነበር ?

7. በቁጥር 26 ላይ ያለው መጥፎ ዜና ምን ድነው?

**ገለጻ**:

የብዙሃን ውሳኔ ሁልጊዜ ትክክል ሊሆን እንደማይችል በዚህ ክፍል ማየታችን አስገራሚ አይመስላችሁም? በቁጥር 12 ብዙኃኑ ጉዞአቸውን መቀጠል እንዳለባቸው እንደወሰኑ እንመለከታለን፡፡ አደጋው በፊታቸው ተጋርጦ ሳለ ፣ማስጠንቀቂያ ቢነገራቸውም እንኳን ብዙኃኑ ወደ ፊት ለመጓዝ ወሰኑ፡፡ በዚህ ምክንያት ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ተጓዦች በሙሉ በተፈጠረው ሁኔታ ተስፋ ቆርጠው ነበር፡፡ በማዕበሉ ይናወጥ የነበረውንም መርከብ ከመስመጥ ለመታደግ ጸንቶ እንዲቆም ለማድረግ በገመድ አሰሩት፡፡ ተጓዦቹ በሙሉ በጣም ተርበው ነበር፡፡ የጭነት የነበረችውን መርከብም ጭነት ለማቅለል ጭነቷን ወደ ባህር ይወረውሩ ነበር፡፡ ከዚያም ቁጥር 20 ላይ ያለው ቃል መጣ፡ “ወደ ፊት እንድናለን” የማለት ተስፋ ሁሉ ተቈረጠ፡፡ ተስፋ መቁረጥ በሁሉም ላይ ይነበብ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሊነገር የሚገባው አንድ ቃል ነው እርሱም “ይህ ከመሆኑ በፊት አስቀድሜ ነግሬያችኋለሁ”፡፡ ጳውሎስ እንደዚህ ነበር ያላቸው፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ይህንን ብሏቸው አላቆመም፡፡ ጳውሎስ ከዚህ ሁሉ ፈተና አምልጦ ሮም እንደሚደርስ ጌታ ነግሮታል፡፡ እግዚአብሔርም አብረውት የነበሩት ሰዎች ለጳውሎስ አሳልፎ ሰጥቶት ነበር፡፡ ጳውሎስም እግዚአብሔር የተናገረው ነገር በትክክል እንደሚፈጸም ያምን ስለነበር፤ ይህ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር አልነበረው፡፡

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. ህይወታችሁ በተለያዩ ማዕበሎች የተናወጠበትን ጊዜ ተረጋግታችሁ መኖር ያቃታችሁ ጊዜ በህይወታችሁ አጋጥሟችሁ ያውቅ ይሆን?

___

___

2. የብዙኃኑን ውሳኔ ሰምታችሁ እንደ ልጅ፣ እንደ ህዝብ፣ እንደ መሪ ወይንም ተመሪ የተጓዛችሁበት የህይወት ልምምድ ይኖራችሁ ይሆን?

___

___

3. የብዙኃን ውሳኔ እምነታችሁን ወይንም ውሳኔያችሁን እንድትለውጡ ያስገደዳችሁ ወቅት ይኖር ይሆን? አጋጥሟችሁ ከሆነ በምን አይነት ሁኔታ?

___

___

**<u>ክፍል 5</u>**

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 27:27-44 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ለአስራ አራት ቀናት ያክል መርከቡ በባህሩ ላይ በማዕበል ሲንገላታ ነበር፡፡ መርከበኞቹ ወደ ምድር የደረሱ መስሏቸው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት መርከቡ ከአለት ጋር ተጋጭቶ መሰበሩ ስለማይቀር በታንኳዎች መርከቡን ትተው ሊያመልጡ አስበው ነበር፡፡ ጳውሎስ ለመቶ አለቃውና ለወታደሮቹ ምን ነገራቸው(ቁጥር 31)?

___

___

ስለዚህ በመጨረሻ ወደ ባህር የተጣሉት ታንኳዎቹ ናቸው፡፡

ጳውሎስ________________________ አበረታታቸው (ቁጥር 33)፡፡ ጳውሎስ አንዳቸውም እንዳማይሞቱ በመንገር በህይወት እንዲቆዩ ምግብ መብላት እንደሚገባቸው ነገራቸው፡፡ ከዚያም ዳቦ አንስቶ በፊታቸው አስግኖ ቁርሶ በላ፡፡ ይህንን ማድረግ በጣም

ቀላል ነገር ሊመስል ይችላል! ጳውሎስ ይህንን ያደረገው ሌሎቹም አይተው እንዲበረታቱ እንዲመገቡም ለማድረግ ነው፡፡ ምን ያህሉ ነበሩ የተመገቡት? __________

2. ምግብ ከተመገቡ በኋላ ምን ነበር ያደረጉት (ቁጥር 38)?

_______________________________________________

3. እኩለ ቀን ላይ ምን ሆነ (ቁጥር 39-44)?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. ልክ ጳውሎስ ይሆናል ብሎ እንደተናገረው መርከቡ በዲብ ላይ ነዱት፡፡ ከዚያስ ወታደሮቹ ምን ሊያደርጉ አሰቡ (ቁጥር 42)?

_______________________________________________

5. የመቶ አለቃው ውሳኔ ምን ነበር (ቁጥር 43)?

_______________________________________________

አንዳንድ ሰዎች ከመርከቡ ላይ ይዘሉ ጀምር አንዳንዶች ደግሞ በመርቡ ስብርባሪ ላይ ተንሳፈፉ፡፡ በዚህ ሁኔታ_______________________________ (ቁጥር 44)፡፡

**ማሰላሰል**:

መርከቡ በላዩ ላይ የነበሩትን አዳናቸው(ቁጥር 31)፡፡ መርከቡ ከኋላው ከሚገፋው ነፋስ የተነሳ ተሰባበረ (ቁጥር 41)፡፡ መዋኘት ለማይችሉት የመርከቡ ስብርባሪዎች ለመዳን ምክንያት ሆነላቸው (ቁጥር 44)፡፡ መርከቡ ላይ የተለያየ የማህበረሰብ አባላት የነበሩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል መርከበኞች፣እስረኞች፣ወታደሮችና የጦር መኮንኖችን ይገኙበታል፡፡ በመርከቡ ላይ የነበሩት ሰዎች አጠቃላይ ብዛት 276 ሲሆን ከመካከላቸው አንድም የሞተ አልነበረም ፡፡ እነዚህ ሰዎች የነበሩበት ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዙሪያቸው የነበረው ሁኔታ ከባድ ሲሆን ማዕበሉም ሆነ ዲቡ መርከቡን እየሰባበሩት ነበር፡፡ መርከቡ የአሸዋው ክምር ውስጥ በፊቱ ተተከለ፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ እንደዚህ በማለት ተናገረ፡ “እነዚህ_______________እናንተ_______________አትችሉም አላቸው (ቁጥር 31)፡፡” መርከቡ እነዚህ ሰዎች በማዕበሉ መካከል ጭኖ እየተጓዘ ነበር፡፡ ከ276 ተጓዦች አንድ ሰው እንኳን ሳይሞት ሁሉም ተረፉ፡፡ እግዚአብሔር ከማዕበሉ ጠብቆ ሌላ መርከብ አዘጋጀላቸው፡፡ ምንም እንኳን መርከቡ ቢሰባበርም ስብርባሪውን በመጠቀም እስረኞቹ በሙሉ በስብርባሪው

ተጠቅመው ወደ ምድር መድረስ ችለው ነበር። ለእኛ ደግሞ የተለያዩ የህይወት ማዕበሎች ሲገጥሙን እምነት እንደ መርከብ በመሆን ከማዕበሎች እንድንወጣ ያደርገናል። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መልካሙን ውጊያ እንዲዋጋ ሲጽፍለት፣እምነትንና በጎ ህሊና እንዲኖረው አሳስቦታል። ከዚያም ለዚህ ምሳሌ እንዲሆን የመርከብ መሰበር እንደ ምሳሌ በመጠቀም ነው። ለጢሞቴዎስ እንደዚህ በማለት ነበር የነገረው፡ "አንዳንዶች____________________፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ ________________ጠፍተዋልና (1 ጢሞቴዎስ 1:19) እንደገናም በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6:21 "አንዳንዶች ስለ _________________ ስተዋልና።

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. መልካሙን የእምነት ገድል እንድትጋደሉ የሚያበረታታችሁ በችግር ጊዜ አብሯችሁ ቆሞ የሚያበረታታችሁ ማነው?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

2. ህይወት በማዕበል ስትከበብ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እምነት ፀንተን እንድንኖር ያደርገናል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሊያበረታቷችሁ ሊያጸናችሁ የሚችሉ ሰዎች በዙሪያችሁ ሊኖሩ ይገባል።
3. ሌሎች በእምነት ጸንተው መልካሙን ገድል ይጋደሉ ዘንድ መርዳት የምትችሉበትን እድል ፈልጉ።

**የቤት ሥራ**: የሐዋሪያት ሥራ 28 አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ደሴቲቱ______________________ነበረች (ቁጥር 1)። ሁሉም ሰው ወደ ባህሩ ዳርቻ ደረሰ።
2. ስለደሴቲቱ ነዋሪዎች ምን ተነገረን (ቁጥር 2)?

   ______________________________________________________________________

3. በጳውሎስ ላይ ምን ሆነበት ቁጥር 3-6?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

   የደሴቷ ነዋሪዎች ስለ ጳውሎስ ምን አደረጉ (ቁጥር 6)?

   ______________________________________________________________________

4. ፑፐልዮስ ማን ነበር (ቁጥር 7) ምን አደረገ?

5. በመላጥያ የጳውሎስ አገለግሎት ምን ነበር (ከቁጥር 8-9)?

6. ከሶስት ወር በኂላ የባህር ጉዞአቸው አበቃ፡፡ ስለመርከቡ ምን የምናውቀው ነገር ይኖራል (ቁጥር 11)?

7. ከሰራኩስም ወደ ሬጊዩም ከዚያም በፑቲዩሉስ ሄዱ ከዚያስ በኂላ በመጨረሻ ________ደረሱ፡፡

   በዚህ ረጅምና አስቸጋሪ ጉዞ ውስጥ ምን ነበር ጳውሎስን ያበረታው (ቁጥር 15)?

   በሮም የጳውሎስ የኑሮ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

**ክፍል 6**

**ትምህርት**:

እነሆ በመጨረሻ ጳውሎስ ሮም ደረሰ፡፡ በዚያ ዘመን አሁን እንደ አሁኑ ፈጣን ጄቶች፣ ወይንም ፈጣን መርከቦች አልነበሩም፡፡ ስለዚህ እስረኞቹ በዚህ መንገድ ሊጓጓዙ ግድ ነበር፡፡የጳውሎስ ህይወት በሰንሰለት አስረው በሚወስዱት ሰዎች ቸርነት ስር ነበር፡፡ በሮም የነበረው ሁኔታ ጳውሎስ ያስተምር ዘንድ ጥሩ እድል ፈጠረለት፡፡ በመጀመሪያ ያገኛቸው ቡድኖች የአይሁዳውያኖች ቡድኖች ነበሩ፡፡ ትምህርቱን የጀመረው የግል ህይወቱን ምስክርነት በመስጠት ነበር፡፡

ምን ነበር የነገራቸው?

1. በቁጥር 17:

2. በቁጥር 17:

3. በቁጥር 18:

4. በቁጥር 19:

5. በቁጥር 19:

በቁጥር 20 መሰረት ጳውሎስ በሰንሰለት የታሰረው ለምን እንደሆነ ነው የሚነግረን?

ይህ ጳውሎስ የሚያወራለት የእስራኤል ተስፋ ምንድነው? እስቲ ቀጥሎ የጠሰጡትን ማጣቀሻዎች ተመልከቱ: የሐዋሪያት ሥራ 26:6፣ 23:6 እና 24:15።

እኛ ከይሁዳ ስለ አንተ ደብዳቤ አልተቀበልንም፥ ____________ አንድ ስንኳ መጥቶ ስለ አንተ ክፉ ነገር አላወራልንም ወይም አልተናገረብህም (ቁጥር 21)። ነገር ግን በየስፍራው ሁሉ የገጠመውን ተቃውሞ ቢሰሙም አሁን እርሱ ሊናገር የወደደውን ሊሰሙት ፈቃደኞች እንደሆኑ ነገሩት።

**መልመጃ**:

1. ጳውሎስ ምን ነገራቸው?

2. በህግና በነቢያት ስለኢየሱስ የተነገረውን በመግለጥ ስለኢየሱስ ምን ነገራቸው? የሐዋሪያት ሥራ 17:3 ተመልከቱ

3. የትምህርቱ ውጤት ምን ነበር (ቁጥር 24-25)?

____________________________________________________

____________________________________________________

4. በቁጥር 26 እና 27 ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ ኢሳያስ በኩል ስለ አይሁድ ህዝብ ምን ብሎ ተናገረ (ኢሳያስ 6:9-10) ?

   ሀ. ____________________ ትሰማላችሁ ____________________

   ለ. ____________________ ታያላችሁ ____________________ በላቸው።

   ሐ.____________________ እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም ____________________

   መ.____________________እንዳያስተውሉ፥ተመልሰውም____________________፥

   ሠ. የዚህን ሕዝብ ልብ ______________________________

   ረ.ጆሮአቸውንም ________________________________________

   ሰ.ዓይናቸውንም ጨፍን አለኝ።____________________________________

   ሸ. ጌታ ሆይ፥ ________________________? አልሁ።

   ቀ. ቤቶችም ________________እስኪሆኑ ምድርም ፈጽሞ____________ድረስ፥

5. ከዚያም ትልቁ "እንግዲህ"፡ ለመሆኑ ጳውሎስ እነዚህ የአይሁድ መሪዎች እንዲያውቁት የፈለገው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 28)?

   ____________________________________________________

   ____________________________________________________

   "እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ድነት ለአሕዛብ እንደ ተላከ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል!"

6. ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ _______________ ነበር፤ማንም _______________ የእግዚአብሔርን መንግሥት _______________ ስለ _______________እጅግ _______________ ______________ ነበር (ቁጥር 30-31)።

**ማሰላሰል**: የሐዋሪያት ሥራን መጽሐፍ የተጠናቀቀ ሲሆን ይህንን መጽሐፍ ከብዙ ጥያቄዎች ጋር እንደመድመዋለን። የጳውሎስ መከራ አበቃ ይሆን? ከእስር ቤት ወጣ ይሆን? በሮማውያን ከእስር ተፈታ ይሆን? በዚያው በሮም ሞቶ ይሆን? ምን አግኝቶት ይሆን? ሉቃስ ይህንን ጉዳይ እንደ ትልቅ ነገር ቆጥሮ አለመዘገቡ የሚደንቅ ነው። ምናልባት ሉቃስ

ይህንን ጽፎ ለቴዎፍሎስ የላከለት ውሳኔ ከማግኘታቸው በፊት ሊሆን ይችላል (የሐዋሪያት ሥረ 1:1)። ቴዎፍሎስ ከአህዛብ ወገን ነበር። ይህ ሰው ሉቃስ ሁለቱንም መጽሐፍቶቹን ማለትም የሉቃስ ወንጌልንና (ሉቃስ 1:1-4) የሐዋሪያት ሥራን (የሐዋሪያት ሥራ1:1) የጻፈለት ሰው ነው። ሉቃስ ለዚህ ሰው እነዚህ ጽሑፎች የጻፈለት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የድነት የምስራች ወይንም ወንጌል ለአህዛብም ሆነ ለአይሁድ ፣ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሆነ እንዲያውቅ ማድረግን ታሳቢ አድረጎ ነው። የምሥራቹ ኃኪም ለነበረውም ለሉቃስ እንደዚሁም ለቴዎፍሎስ ነበር። እናንተም አህዛብ ብትሆኑ ወይንም አይሁድ ይህን የምሥራቹ ለእኔና ለእናንተም ነው። ለወንጀለኛውም ለንጉሱም፣ለሃብታሙም ለድሃውም፣ለታመመውም ሊሞት ላለውም በአጠቃላይ ለሁሉም ነው። ኢየሱስ ለሁሉም ነው! ስለዚህ ሁላችንም እንደ አህዛቦች ሆነን እንስማው! ሁላችንም እንደ ጳውሎስ በግልጽና ያለመከልከል የእግዚአብሔርን መንገሥት ለሰዎች እንግለጥላቸው በድፍረት ስኢየሱስ እንንገራቸው!

**ጸሎት**:

ኦ የሰማይና የምድር ጌታ እግዚብሔር ሆይ "ግሩምና ድንቅ" አድርገህ እያንዳንዳችንን ፈጥረኸናል (መዝሙር 139:14)። አንተ ሁላችንን የራስህ ልታደርገን ፈጥረኸናል ነገር ግን ኃጢአት ከአንተ ጋር እንዳንሆን ከአንተ ሊያርቀን ይታገለናል። ለእኛ ያለህን ፍቅር በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ገልጸህልናል። ከፍቅርህ የተነሳ አንድያ ልጅህን ሳትሳሳ አዳኝ ይሆነን ዘንድ ሰጠኸን (ዮሐንስ 3:16-17)። ፍቅርህ ደግሞ እውነተኛ እና ምንም አይነት አድልዎ የሌለበት ለሰዎች ሁሉ እኩል ነው። (ሮሜ 10:12-13)። ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድና እውነትን ወደማወቅ ይመጡ ዘንድ ፍላጎትህ እንደሆነ አስታውቀኸናል (1 ጢሞቴዎስ 2:3-6)። በማመናችን ምክንያት መንፈስህ በውስጣችን ይኖራል። በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የገለጥክልን ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ እናውቅ ዘንድ አብርሆቱን ይሰጠናል። የኃጢአታችንን ዋጋ በልጅህ በኢየሱስ ከፍለህልናል ጠላታችንንም ድል ነስተህ ባለ ድል አድርገኸናል። ስለዚህም ምስጋናዬን ሳልቆጥብ ለአንተ እሰጣለሁ። የማስታረቅን ቃል ሰጥተህ የላከኝ የአንተ አምባሳደር መሆኔን አውቄ ልኑር (2 ቆሮንቶስ 5:17፤ 20-21)። በፊትህ ጻድቅ ሆኜ እኖር ዘንድ ኃጢአት የሌለበትን ለእኔ ኃጢአት እንዲሆን አድርገኸዋልና!

**በመጨረሻም**:  ከብዙ ዘመናት ጀምሮ አማኞች እምነታቸውን በሐዋሪያት የእምነት መግለጫ መግለጻቸውን ቀጥለዋል። ይህ በሐዋሪያት የእምነት መግለጫ ውስጥ የተገለጠው እውነተ የሐዋሪያት ሥራ ጥናታችንን ያጠቃልልልናል።

## የሐዋሪያት የመእምነት መግጫ

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።

ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተጸነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ፣ በጴጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፤በተሰቀለ፣በሞተ ፣በተቀበረ፣ ወደ ሲኦልም በወረደ ፣በሶስተኛውም ቀን ከሙታንም በተነሳ ፣ወደ ሰማይም በአረገ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፤ በህያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣በቅዱሳን አንድነት ፣በኃጢአት ስርየት፣ በሥጋ ትንሳኤ፤በዘላለም ህይወት አምናለሁ። አሜን !

## የምዕራፍ ክለሳ

# ኃይላችን የእግዚአብሔር መንፈስ

## ክለሳ

እንኳን ደስ ያላችሁ! *"ኃይላችን የእግዚአብሔር መንፈስ"* የሚለውን የጥናት ክፍል አጠናቃችኋል፡፡ በኢየሩሳሌም ያደገችውና በስደት ወደ ይሁዳ፣ሰማሪያ እና ሮም የተስፋፋችው የቀድሞዋን ቤተ ክርስቲያን በደንብ ተዋውቃችኋታል፡፡ አብረው በአንድነት እንዴት ያመልኩ እንደነበር፤ እንጀራ በመቁረስ አብረው በጸሎት እንዴት ይተጉ እንደነበር ተምራችኋል፡፡ ለአይሁድና ለአህዛብ ወንጌል ያደረሱትን የቤተ ክርስቲያን አእማድ የነበሩትን ጴጥሮስና ጳውሎስን ተዋውቀናቸዋል፡፡ ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን እንደ መልህቅ ጸንታ እንድትቆም ያደረገ ሲሆን ጳውሎስ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን እየተላከ ሚሲዮናዊ ጉዞዎችን አድርጓል፡፡ ስደት ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ተፈታትኗት እንደነበረ ጳውሎስን ፣በርናባስን እና ሲላስን የመሳሰሉ ሰዎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል በተንቀሳቀሱባቸው ጊዜያት ሁሉ በድንጋይ ሲወገሩ፣ሲታሰሩ ፣ሲገተቱ እና እንደሞተ ሰው ሲጣሉ ተመልክተናል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች በትጋትና በድፍረት ሰረገላዎች ላይ እየወጡ ፣በምኩራብ እየሄዱ ቤት ለቤት እየሄዱ፣ ሰዎችን ለክርስቶስ ሲማርኩና ሲያጠምቁ ተመልክተናል፡፡ ንሰሃና የኃጢአት ስርየት ለሰው ሁሉ እንደተዘጋጀ በማመን ህይወታቸውን ለዚህ እውነት ሰጥተው ነበር የኖሩት፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው እንዲሆን ሰጣቸው ታማኝ ደ ቀመዛሙርቱ እንዲሆኑ እንደዚሁም በታማኝነት ለዓለም እንዲመሰክሩ አስታጠቃቸው፡፡

የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ሰዎች የክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ምሥክር ይሆኑ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ልብ ሲለውጥ በሚያሳይ እውነት ነው የሚጀምረው፡፡ ይህ ወንጌልን የማድረስ ስራ አማኞች በማህበረሰቡ ውስጥ እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸው እንዲጨምር አድጓል፡፡ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሰዎችን ሲጠቀም እንመለከታለን፡፡ በማቴዎስ 28፡19-20 ባለው ክፍል በተጻፈው መሰረት ወንድና ሴቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እለት እለት ይጨመሩ ነበር፡፡ ይህ ክፍል ሰዎችን እንድናስተምር፣እንድናጠምቅ፣እና ደቀ መዛሙርት እንድናደርጋቸው የሚያስታውሰን ታላቁ ተልዕኮ ነው፡፡

አሁን የክለሳ ግዜያችሁ ነው፡፡ አስታውሱ እነዚህ ጥያቄዎች እናንተን ለመፈተን ሳይሆኑ ጥናታችሁን ምን ያህል እንደተከታተላችሁ ለመመዘን ያክል የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በዮሐንስ 20፡21 ላይ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የተናገረውን ነገር አስታውሱ፡ “አብ______________________እኔ ደግሞ ______________________ አላቸው፡፡” የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ለመቀበል ሥለተጠራችው ቀደምት ቤተ ክርስቲያን ጥቂት በክለሳ መልክ እንመልከት፡፡*መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ከክርስቶስ ጋር ለማገናኘት ማንን እንደተጠቀመ አስታውሱ፡*

| የመጽሐፍ ቅዱስ ክፊል | ማነው የተላከው? | ታሪኩ ምን ነበር? |
|---|---|---|
| የሐዋሪያት ሥራ 1:8 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 2:1-13 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 3:1-10 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 6:1-7 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 8:26-40 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 9:1-19 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 10 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 13:1-3 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 16 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 23-26 | | |
| የሐዋሪያት ሥራ 28:17-31 | | |

በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንኖር እምነታችንን ለሌሎች የምናካፍልበት እድል እናገኛለን። በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ተሰቀለውና ስለሞተው ደግሞም ስለተነሳው መሲህ ያላቸውን እውቀት እና እምነት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለሌሎች ሲያካፍሉ እንመለከታለን። ሁሉም ከራሳቸው ልዩ ከሆነ ልምምዳቸው ነበር የሚያካፍሉት። እያንዳንዱ ስለ እውነት ይመሰክራሉ። እያንዳንዱ በህይወታቸው እንደሚሰራው የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል መጠን ወንጌልን በግልጽ ይመሰክሩ ነበር። ወንጌልን ለመናገር ያልተዘጋጀ ሰው አልነበረም። ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ተስፋ ያለማወላወል ይናገሩ ነበር። እውነቱን ለሰዎች ለማካፈል ከፍተኛ ጉጉት ነበራቸው። የሚኖሩት የሰሙትና ያዩትን እንዲመሰክሩ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለማሳካት ነው (የሐዋሪያት ሥራ 4:20)።

በእናንተ ስላለ ______________________________ ምክንያትን ________________________ለመስጠት ዘወትር ___________________ ሁኑ፥ ነገር ግን __________________ _________________ ይሁን። (1 ጴጥሮስ 3:15)።

እናንተስ እስቲ በውስጣችሁ ስላለው ተስፋ ያላችሁን ምስክርነት ግለፁ።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

**ጸሎት**:

ምስክሩ እንድትሆኑ በላካችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላችሁ ድፍረት እና ብርታት፣እናም ታላቁን ተስፋ መናገር የምትችሉበትን ጥበብ በሚያስታጥቃችሁ መንፈስ ቅዱስ (ማቴዎስ 10:19-20)፣እግዚአብሄር አብ ከእርሱ የተማራችሁትን እውነት በድፍረት እና በግልገጽ መመስከር የምትችሉበትን እድል እንዲሰጣች ጸልዩ

ተጨማሪ የክሮስ ኮኔክት ጥናቶች በነፃ ከድህረ ገፃችን ይገኛሉ።

የአገልግሎታችንን ድህረ ገፅ: www.crosscm.org.

አስተያየታችሁን መስማት እንፈልጋለን!

በዚህ አድራሻ እንገናኝs: admin@crosscm.org